በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የመቐለ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደብዳቤ ቁጥር Vpss/0238/10 በቀን 08/04/2010 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ ሪፖርት የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በዩኒቨርሲቲው የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፤
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፤

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. **የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብን በተመለከተ**

   የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/ሀ የሂሣብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት፤ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው በሚገልፀው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በጤና ሣይንስ ኮሌጅ ብር 43,201.04፤ በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 19,208.74፤ በድምሩ ብር 62,409.04 /ከግል ሕክምና አገልግሎት የተገኘው ገቢ ሰኔ 30 በተደረገው ቆጠራ በገንዘብ ያዡች እጅ የተገኘ ሲሆን ዓመታዊ ሪፖርቱ ላይ የሚታይ ጥሬ ገንዘብ የሌለ መሆኑ፤

2. **<u>የገቢ ሂሳብን በተመለከተ</u>**

   በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/ሀ የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን

ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት፤ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 4 መሠረት መመሪያዎቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዓይደር ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ከግል ሕክምና አገልግሎት መስጫ ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ለገ/ኢ/ል/ት/ ሚ/ር ሪፖርት መደረግ የነበረበት ብር 82,224,535.69 ሲሆን ሪፖርት የተደረገው ብር 67,567,804.67 ብቻ በመሆኑ ልዩነት ብር 14,656,731.02 በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤

❖ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ወጪ የተደረገው ብር 73,984,652,12 ሲሆን ለገ/ኢ/ል/ት/ ሚ/ር ሪፖርት የተደረገው ደግሞ ብር 65,097,129.44 በመሆኑ ብር 8,887,522.68 በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤

3. ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ፈተና ለፈተኑበት ከድርጅቶቹ በአጠቃላይ ብር 400,506.91 ገቢ የተገኘ ሲሆን ለመምህራንና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች 80% ብር 356,127.82 የተከፈለ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው 20% ብር 44,379.09 ገቢ እንዲሆን በዩኒቨርሲቲው ሴኔት በተወሰነው መሰረት የተፈፀመ እና የተገኘ ገቢ ለመምህራኑና የመንግስት ድርሻ የክፍፍሉ መጠን (Rate) በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይወሰንና ክፍፍሉም በቦርድ ሳይጸድቅ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡

4. ዩኒቨርሲቲው በሥራ እንቅስቃሴው የሚሰበስባቸው ገቢዎች የመንግስት ደንብና መመሪያን ተከትሎ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

❖ በሪፈራል ሆስፒታል የዱቤ ህክምና አገልግሎት ውል ከገቡ ተቋማት አገልግሎት ላገኙበት ክፍያ ብር 1,120,001.90 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

❖ ከንግድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ መሰብሰብ የነበረበት ብር 558,473.54 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

- ❖ በዓይደር እና በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከንግድ ቤቶቹ ብር 2,393,188.37 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ የሚታይ ሲሆን ስለመሰብሰቡ ለማጣራት ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፡
- ❖ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ዓመት ድረስ ያልተሰበሰበ ከ 3 ተከራዮች (ግርማይ በርሀ የልብስ ስፌት፤ ፀጋ ገ/ስላሴ /ጃምቦ/ ካፌና ሬስቶራንት እና ሙሉ ብርሃነ ካፌና ሬስቶራንት) ስለሚፈለገው የገቢ ሂሳብ ብር 1,982,522.30 ጉዳዩ ለህግ ክፍል የተመራ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ምንም እርምጃ ሳይወሰድ የሚገኝ ሲሆን

በጠቅላላው ብር 6,054,186.11 ውዝፍ የገቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

<u>የወጪ ሂሳብ በተመለከተ፤</u>

5. ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ የክፍያ ተመን ሳይኖረው ለኤግዛማይነር
   - ➢ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 369,280.00
   - ➢ የተፈጥሮ ሳይንስና ቀመር ኮሌጅ ከመደበኛ በጀት ብር 336,000.00
   - ➢ የህብረተሳብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 1,705,000.00
   - ➢ የእንስሳት ሳይንስ ሕክምና ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 186,700.00
   - ➢ የሕግና የሥነ -መንግሥት ኮሌጅ ከመደበኛ በጀት ብር 321,000.00
   - ➢ የቢዝነስና ኢኮኖሞክስ ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 161,500.00
   - ➢ የህፀተ ዝናብና ግብርና ኮሌጅ ብር 91,800.00

   በድምሩ ብር 3,171,280.00 ተመን ሳይኖረው የተከፈለ መሆኑ
6. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ‹‹ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ እንዳሳሰበ›› መመሪያው ቢያመለክትም፤
   - ❖ በኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የAdhoc ኮሚቴ በሚል ብር 39,000.00 የተከፈለ መሆኑ
   - ❖ በህግና ስነ-መንግስት ኮሌጅ የኮሚቴ ክፍያ በሚል ብር 52,400.00 የተከፈለ መሆኑ፤

በጠቅላላው ድምር ብር 91,400.00 አላግባብ ለኮሚቴ ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል

7. የውጪ መምህራን የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ጥቅምት 2001 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2.2.12 የተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በሚለው ስር ‹‹የውጪ መምህራን ያላቸውን ሙያና የአካዳሚክ ደረጃ መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባውን የደመወዝ መጠን በተመለከተ በመደራደር ይወሰናል፡፡ ይህ የደመወዝ መጠን በትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክና ደረጃ ከተቀመጠው ጣሪያ (Scale) በላይ መሆን እንደሌለበት›› መመሪያው ቢያመለክትም

በዋና ግቢ

❖ ዩኒቨርሲቲው ለውጭ አገር መምህራን ባላቸው የሙያና የአካዳሚክ ደረጃ መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባውን የደመወዝ መጠን ትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክና ደረጃ ካስቀመጠው ጣሪያ (Scale) በላይ ለ16 መምህራን በድምሩ $ 37,590.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤

8. በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 4 ማንኛውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚገኘው ጠቅላላ የወር ገቢ ላይ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት ግብር መክፈል እንዳለበት እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸ ቢሆንም፤

❖ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጪ ሀገር መምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ16 የውጪ ሀገር መምህራን የደመወዝ ክፍያ ሲፈፀም የሥራ ግብር ብር 1,042,683.10 መቀነስ እያለበት ሳይቀነስ የተከፈለ መሆኑ፣

❖ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ከፈረንሳይ እና ከህንድ ለሚመጡ መምህራን የማስተማር /የምርምር አገልግሎት ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ቀን አንስቶ ከሁለት አመታት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነፃ መሆናቸውን መመሪያው ቢያመለክትም፤ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ የተቀጠሩ የህንድ ሀገር መምህራን ከግብር ነፃ የሚሆኑበት የጊዜ ገደብ ካለቀ በኃላ ለ39 የህንድ መምህራን የሥራ ግብር ከ7 ወርእስከ 9 ዓመት ባለው ጊዜ መክፍል ያለባቸውን የሥራ ግብር ያልከፈሉ ሲሆን በናሙና ከታየው ውስጥ የግንቦት

እና የሰኔ /2009 ብር 4,115,511.65 የተከፈላቸው ቢሆንም የሥራ ግብር ብር 1,323,429.08 መቀነስ እያለበት ሳይቀነስ የተከፈለ በመሆኑ፣ በጠቅላላው ብር 2,366,112.18 ያልተቀነሰ የሥራ ግብር መኖሩ፤

9. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና አፈፃፀም በመስከረም /2004 ዓ.ም ላይ በክፍል ሰባት በአንቀፃ 7.2 በንፅስ አንቀፃ 7.1.8 ለማስተር ድግሪ ከሃያ አራት ወር (2 ዓመት) ለዶክተሬት ድግሪ ከአራት ዓመት መብለጥ እንደሌለበት ከበለጠ ግን እድሉን የሰጠው ተቋም ማረጋገጥ እንዳለበት›› በሚያመለክተው መሰረት ስለመሰራቱ እንዲሁም በጊዜ ገደባቸው ስለመመለሳቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በዋናው ግቢ

በዩኒቨርሲቲው በሀገር ወስጥ እና ከሀገር ወጭ ውል ገብተው ለት/ት ወደ ውጪ ሀገር ከተላኩት መምህራን መካከል ለሁለተኛ ዲግሪ 9 ለሦስተኛ ዲግሪ 22 በድምሩ 31መምህራን ከላይ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመለሱ ሲሆን አካዳሚክ ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ሳይቀርብ በበጀት ዓመቱ ብር 499,693.50 የደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ወጪ ሆኖ የተከፈለ መሆኑ፤

10. አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን መቀጣታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የህንፃ ስራው ለዘገየበት ከ 2 የስራ ተቋራጮች ላይ በዋናው ግቢ መሰብሰብ የነበረበትና ያልተሰበሰበ ብር 527,041.04 ከተለያዩ የእቃ አቅራቢዎች በወቅቱ እቃውን ገቢ ባለማድረጋቸው ብር 3,395,373.68 በጠቅላላው ብር 3,922,414.72 መክፈል የሚገባቸው የጉዳት ካሳ ያልከፈሉ መሆኑ፤

11. በውሉ መሰረት አቅራቢዎቹ ዕቃውን አጠናቀው ገቢ ማድረግ ባለባቸው ቀኖች ስላላስገቡ ላዘገዩበት ከድርጅቶቹ የተቀነሰው ከዋናው ግቢ ብር 1,236.61፤ ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 337,408.28 በድምሩ ብር 338,644.89 የጉዳት ካሳ ተቀንሶ በ1489 ሂሳብ መደብ ላይ የተመዘገበ ቢሆንም የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ፤

12. የዩኒቨርሲቲው የግዥ ክፍል የመንግስትን ወጪ ሊቀንስ በሚችል መልኩ የግዥ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ አውጥቶ በርካታ ድርጅቶችን በማሳተፍ የመንግስት ጥቅም ማስጠበቅ ሲገባ፣

- በዋናው ግቢ ብር 700,150.72 በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 797,527.92 በድምሩ ብር 1,497,678.64 በናሙና ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ፣ ግዥን በመቆራረጥ ክፍያ የተከናወነ መሆኑ፤

13. ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት ዋናው ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው፤

- በዋናው ግቢ በቀን 24/9/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 178165 በሂሳብ መደብ 6211 ከአንበሳ ጫማ አክስዮን ማህበር ጫማ ለተገዛበት ብር 912,775.86 ሲከፈል መቅረብ ያለበት የሽያጭ ደረሰኝ (cash sale invoice) መሆን ሲገባው፣ እንደ ሽያጭ ደረሰኝ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (Cerdit sale invoice) ቀርቦ ሂሳቡ የተወራረደ መሆኑ፤
- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የቢሮ እቃዎች መደርደሪያ ሽልፍ ለመግዛት በ11/11/08 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 446377 ለሙሉ ክብሮም ዛፉ የቢሮና የቤት እቃዎች አቅራቢ ለተከፈለ ብር 891,809.75 የሽያጭ ደረሰኝ ሳይቀርብ በAttachement Cash Sales invoice ብቻ ሂሳቡ የተወራረደ መሆኑ፤

14. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዋና ግቢ ብር 13,660,905.78
- በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 7,943,271.52
- በተፈጥሮ ሳይንስና ቀመር ኮሌጅ ብር 122,940.00
- በህብረተሳብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ ብር 1,869,559.95
- በሕግና የሥነ -መንግሥት ኮሌጅ ብር 17,726.23

በድምሩ ብር 23,616,403.48 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ ገንዘቡ ተከፍሎ እና ሂሳቡ መመዝገቡ፤

15. የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት ለመከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፡

- ❖ በዋና ግቢ ብር 2,173,916.00
- ❖ በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 2,645,239.09
- ❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 124,680.00
- ❖ በመቐለ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 364,353.62
- ❖ በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 322,408.04

በድምሩ ብር 5,630,596.75 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ መሆኑ፣

16. ዩኒቨርሲቲው በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የሰጣቸውን ክፍያዎች በወቅቱ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲና ቅድስትና መስፍን ደረቅ እንጀራ መጋገርና ማቅረብ ሕ/ሽ/ማህበር ጋር እንጀራ ለመጋገር በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት ውል ያሰሩት ከመስከረም 21/08 - ሰኔ 30/08 ሲሆን አቅራቢዎቹ በቀን 30/12/08 እና 13/01/09 በማመልከቻ ቅድሚያ ክፍያ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት ተፈቅዶላቸው በደረሰኝ ቁጥር 289440 ብር 27,147.71 እና በደረሰኝ ቁጥር 289452 ብር 38,457.76 የወሰዱ ቢሆንም ከቀጣይ ክፍያ ላይ በቅድሚያ የወሰዱት ብር 65,605.47 መቀነስ ሲገባው ሳይቀነስ ብር 143,415.00 ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፤ እንዲሁም ቅድሚያ ክፍያው ሲፈቀድላቸው ውል ያላደሱ መሆኑ፤

17. በፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 5 አንቀጽ 25 .3 መሠረት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን በቴክኒክ ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ከመጀመሪያው ውል ተነጥለው ሊሰሩ የማይችሉ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎችን ግንባታውን እያከናወነ ከሚገኘው ሥራ ተቋራጭ መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት ከመጀመሪያው ውል ጋር ሲነፃፀር ከ30% የማይበልጥ ተጨማሪ የግንባታ ሥራ ማሠራት እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በዋናው ግቢ በኤ.ቲ.ኤስ ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግል ማ.የካፍቴሪያ ብሎክ የቫውቸር ቁጥር 0717927 በቀን 06/06/09 ከመጀመሪያው የውል ጠቅላላ ዋጋ ብር10,885,260.37 ብር 3,265,578.11 የዋጋ ጭማሪ ማድረግ ሲገባ ብር 5,570,358.16 ተጨማሪው የግንባታ ሥራ እንዲሰራ በመደረጉ አላግባብ ብር 2,304,780.05 የዋጋ ጭማሪ ተደረጎና ተከፍሎ መገኘቱ፤

18. **የተሠብሣቢ ሂሣብ በተመለከተ፤**

- ከመደበኛ በጀት ብር 22,723,053.64 ከውስጥ ገቢ ብር 24,762,558.02 በድምሩ ብር 48,485,611.66 ከ1996 እስከ 2009 በጀት ዓመት በቅድሚያ ክፍያ የተመዘገበ ሂሳብ /ከ6ወር እስከ 14 ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተከፈለና በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ሳይወራረድ የሚገኝ መሆኑ፤
- ተቋሙ ለግንባታ ሥራ ለ1 ሥራ ተቋራጭ ፤ ለ1አማካሪ መሐንዲስ ፤ ለ1 ዕቃ አቅራቢ ድርጅት በድምሩ ብር 13,147,342.97 ለተከፈለ ቅድመ-ክፍያ የዋስትና ማስያዣ /ማስከበሪያ/MAY3, 2001 (ሚያዝያ 25,2003 ዓ.ም እስከ NOVEMBER,2012 (ህዳር, 2005ዓ.ም) ገንዘብ ብር 13,235,517.65 የቀረበው የጊዜ ገደቡ ያለፈ መሆኑን እና በውሉ መሠረት አቅራቢዎቹ ላልሰጡት አገልግሎት፤ ላላጠናቀቁት ሥራ በሕግ የተጠየቁበት እና ውሳኔ የተገኘበት ማስረጃ የተቋሙን ጥቅም ከማስከበር አንፃር በውል ተቀባይ ተዋዋይ ወገኖች ላይ የተወሰደ እርምጃ ባለመኖሩ ሂሳቡ ከ5 ዓመት እስከ 9 ዓመት በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዙን፤
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል በ4210 ሂሳብ መደብ ተቀጽላ ሌጀር ቁጥር D01 በ2009 በጀት ዓመት በመክፈቻ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲዞር እና በተዘጋ የሂሳብ ሪፖርት በመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የሂሳብ ምዝገባ ላይ ብር 6,937.43 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሂሳብ ሚዛን መታየት የሚገባው በክሬዲት የሂሳብ ሚዛን መታየቱ፤

19. **የተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ፤**

    - የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ከ6 ወር እስከ 13 ዓመት ድረስ ያሉ ተከፋይ ሂሳቦች ከመደበኛ ሂሳብ ብር 17,361,577.02 ከውስጥ ገቢ ብር 265,322.01 በድምሩ ብር 17,626,899.03 በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱ፤

20. **መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን የታየ ተከፋይ ሂሳብ**

<u>ከመደበኛ ሂሳብ</u>

በዓመታዊ የመዝጊያ ሂሳብ ሪፖርት ላይ እንደሚታየው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ በ5059 ሂሳብ መደብ በክሬዲት ሂሳብ ሚዛን መታየት የሚገባው ሂሳብ ብር 310,757.49 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን ላይ መታየቱ፡-

ከውስጥ ገቢ ሂሳብ

በዓመታዊ የመዝጊያ ሂሳብ ሪፖርት ላይ እንደሚታየው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ በ5059 ሂሳብ መደብ በክሬዲት ሂሳብ ሚዛን መታየት የሚገባው ሂሳብ ብር 39,050.00 በድምሩ በዓመታዊ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 349,807.49 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን ላይ መታየቱ፤

በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ

- ❖ በሂሳብ መደብ 5005 ብር 4,461.55፤
- ❖ በሂሳብ መደብ 5006 ብር 8,591.45 በድምሩ ብር 13,053.00 በኮሌጁ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በመደበኛ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት መታየት የሚገባው ሂሳብ በዴቢት የሂሳብ ማዛን ላይ መታየቱ፤

በመቐሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

- ❖ በሂሳብ መደብ 5002 ብር 612,891.96፤ በሂሳብ መደብ 5006 ብር 2,485.42 በድምሩ ብር 615,377.38 በኮሌጁ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በመደበኛ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት መታየት የሚገባው ሂሳብ በዴቢት የሂሳብ ማዛን ላይ መታየቱ፤

21.የበጀት ሂሣብ በተመለከተ

ከመደበኛ በጀት ብር 18,710,110.97፤ ከካፒታል በጀት ብር 1,754,338.25፤ ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 8,917,551.35፤ በድምሩ ብር 29,382,000.57 (11%) ከበጀት በላይ ተጠቅሞ መገኘቱ፤

ከላይ በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች

- ➢ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 143,352.96 የተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው መሆኑ፤
- ➢ የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመርያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፤ ንዑስ አንቀጽ 3 ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወደ መስሪያ ቤቱ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት ተገልጿል፤፤ይሁን እንጂ

- ❖ በየእንስሳት ህክምና ኮሌጅ በቀን13/01/09 በቫውቸር ቁጥር 714561 ለእንስሳት መኖ የሚውል የሳር ክምር ከአበርገለም አለም አቀፍ የእንስሳት ሃብት ልማት በብር 137,662.99 ግዥ ያከናውነ ቢሆንም ዕቃው በሞ/19 ገቢ ሳይሆን ክፍያ መፈፀሙ፤
- ❖ በህግና ስነ-መንግስት ኮሌጅ በቀን 14/10/09 በደረሰኝ ቁጥር 0875875 ለ5ኛ አመት ለህግ ተመራቂ ተማሪዎች በብር 12,000 የመጽሄት ግዥ ያከናወነ ሲሆን መጽሄቱ በሞ/19 ገቢ ሳይሆን ክፍያ መፈፀሙ፤

በድምሩ ብር 149,662.99 በሞ/19 ገቢ ሳይሆን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

ሌሎች ጉዳዮች

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በዓይደር ካምፓስ

- ❖ በዕርዳታ የሚገቡ የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ከሚላኩበት ሀገር /የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች/ ንብረቶቹ ከመላካቸው በፊት የዕቃዎቹ ዓይነት፡ ዋጋ፡ ብዛት የማይታወቅ መሆኑ፡- እንዲሁም በዕርዳታ ገቢ የተደረጉት የሕክምና መገልገያዎች ገቢ በተደረገበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና ወጪ ተደርገው ለአገልግሎት ዝግጁ በሚሆኑበት ንብረት ወጪ ሞዴል ላይ ዋጋቸው የማይገለጽ መሆኑ፡- ለአብነት ያህል የንብረት ገቢ ደረሰኝ /የሞዴል 19/ ቁጥር 17228 ቀን 08/12/08 የንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር 831099(06/10/08) ፣837559(10/10/08)
- ❖ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተካሄደ ቢሆንም የሕክምና መገልገያ መሣሪዎች በኮምፒተር ምዝገባ ከተከናወነውና በቢን ካርድ ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ወይም ልዩነት መኖሩን በቆጠራ ኮሚቴው ያልተረጋገጠ መሆኑን፡-

ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች

- ❖ በ PHARMACOLOGY LAB.
  - PCR SET ከአራት ዓመት በላይ
  - VACUUM OVEN

- ROTARY EVAPORATOR

❖ **STIMULATION LAB.**

- LAPSIM ከ6 ወር በላይ

ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ሁኔታዎች ንብረቶቹ እንደሚገኙ በተደረገው የኦዲት ቅኝትና ዳሳሳ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በቃላሚኖ ካምፓስ

ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች /በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች/

የምግብ ቤትን በተመለከተ

1 ፍሪጅ ከ4ዓመት በላይ፣ 1 ባለስድስት ምድጃ በኤሌክትሪክ የሚሰራ፣ 2 የወጥ መስሪያ ፣

1 የሻይ ማፍያ እና 2 የትሪ ማጠቢያ ከ3 ዓመት በላይ

በ **PARASITOLOGY LAB.**

MICROSCOPES ከ2 ዓመት በላይ ፣ +4 REFRINRATOR ከ3 ዓመት በላይ እና INCUBATOR ከ2 ዓመት በላይ

በ **VET.PATHOLOGY LAB.**

- AUTOMATIC TISSUES ፣ PROCESSOR፣ MICROSCOPES. ፣CHEMICALS

በብልሽት ምክንያት ሳይጠገኑ እንዲሁም መወገድ የሚገባቸው ኬሚካሎች ሳይወገዱ ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ሁኔታዎች ንብረቶቹ እንደሚገኙ በተደረገው የኦዲት ቅኝትና ዳሳሳ ለመመልከት ተችሏል፡

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

- ❖ በተማሪዎች ምግብ ቤት በብልሽት ምክንያት 1 ጀኔሬተር ከ2 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ❖ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን ከ4 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ❖ ፍሪጅ 2 ትልቅ 2 መካለኛ 1 ትንሽ በድምሩ 5 ከ4 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ❖ የሽንኩርት መፍጫ ብዛት 2

- የእንፋሎት መውጫ ብዛት 1 ከ4 ዓመት በላይ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸውን በተደረገው የኦዲት ቅኝትና ዳሳሳ ለመመልከት ተችሏል፡

የንብረት ቆጠራን በተመለከተ

- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም ከመዝገብ ጋር ያለተገናዘበ መሆኑ፡-
- የመጽሐፍት ቆጠራ በዓመታዊው የኢንስቲትዩቱ የንብረት ቆጠራ ያልተካተተ መሆኑ፡-

የንብረት ክምችትን በተመለከተ

- ለማጽጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች ኦሞ፤ ፊሊት የመሳሰሉት በብዛት ተከማችተው በንብረት መጋዘን መገኘታቸው፤
- የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪዎች በፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤
- የነዳጅ መቆጣጠሪያ ልኬታቸው /ጌጅ/የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ብዛት 36 /ሠላሳ ስድስት/የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ /የሌላቸው ብዛት 44 /አርባ አራት/
- በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪ ኮድ ያልሆኑና የተቋሙ ንብረት ስለመሆናቸው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ብዛት 15 /አስራ አምስት/፤
- የሠሌዳ ቁጥር እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ብዛት 2/ሁለት/ መሆኑ፤
- ለተቋሙ የህግ አገልግሎት በተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለማስመለስ በስራ ክፍሉ ተገቢው ክትትል እየተደረገ መሆኑንና ጉዳዮቹም የሚገኙበትን ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ **ለህግ ክፍል ተመርተው ክስ ያልተመሰረተባቸው ጉዳዮች**

በዋናው ግቢ

- ለተቋሙ የህግ አገልግሎት በተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለማስመለስ በስራ ክፍሉ ተገቢውን ክትትል እየተደረገ መሆኑንና ጉዳዮቹም የሚገኙበትን ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ ወደ ተለያዩ ተቋማት ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሰረት ባለመፈፀማቸው (1) ለአንድ መምህር የሚፈለግበትን የዕዳው መጠን ገና ያልታወቀ ፤32 መምህራን ደግሞ ብር 3,490,312.00 ጉዳዩ ለህግ አገልግሎት የተመሩ ቢሆንም ክስ ሳይመሰረትባቸው ያለምንም እርምጃ የሚገኙ መሆኑ

እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣

- ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢዎች በውላቸው መሠረት ሳያስረክቡ ላዘገዩበት አቅራቢዎች ገቢ መሆን የነበረበት ብር 793,337.87 የጉዳት ካሳ ለመንግሥት ገቢ አለመደረጉ
  - ❖ ለላአግባብ የ2006 እና የ2007 ዓ.ም የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ብር 29,564.40 የተሰጠ መሆኑ፤

  <u>በመቀሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት</u>

  - ❖ ለውሎ አበል እና ለሌሎች ጉዳዮች ማስፈጸሚያ በሚል ገንዘብ ብር 2,521.10 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፡-
  - ❖ ቅድመ ገቢ ግብርና ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 34,807.35 ሳይቀነስ ክፍያ መፈፀሙ፤
  - ❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 446122 የመድሃኒት ግዥ ክፍያ ሲፈጸም የብር 243,890.00 መድሃኒቶች የግዥው ዘዴ የተከናወነበትና ውል የተፈጸመበት ማስረጃ ሳይቀርብ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥሮች 18043 እና 16523 mannitol salt agar 50gm, Metris 100ml እና ECG paper for schiler (AT-102) ገቢ ተደርገው ክፍያ ተፈጽሞባቸው መገኘቱ፡-
  - ❖ ተቋሙ የአሳተመው አጀንዳ ጥራቱን ያልጠበቀ መሆኑን የተገለፀ ቢሆንም አጀንዳው በሙሉ ገቢ ተደርጎ ለአገልግሎት እንዲሰራጭ በተወሰነው መሠረት በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 285692 ብር 1,071,984.00 ክፍያ ተፈጽሞበት መገኘቱ፤
  - ❖ ተቋሙ ከትግራይ ክልል ጤና ቢሮ ባደረጉት ስምምነት መሰረት ፕሮግራሙን ላስተባበሩ ለተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊዎችና የአስተዳደር ክፍል ሰራተኞች ተጨማሪ የስራ ጫና /Overload/ በሚል ብር 999,756.00 ከዩኒቨርሲቲው ቦርድ ፈቃድና ዕዉቅና ውጪ የተከፈለ መሆኑ፤

- የሀይደር ሪፈራል ሆስፒታል የንብረት መጋዘን፡-
  - ❖ የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን መቀመጣቸው፣

    -ዲኮስታር የሚባል መሳሪያ፣ በቁጥር 50 ብለድ ትራንስፈር ዲቫይስ የሚባሉ መሳሪያዎች፣

- ጊዜያቸው ያለፈና አገልግሎት የሚሰጡ መድኃኒቶች እና ሌሎችም የህክምና ዕቃዎችና መሳሪያዎች ሞዴል 19 ያልተቆረጠላቸውና ቢን ካርድ ሳይዘጋጅላቸው ከሌሎች ንብረቶች ጋር አብረው መቀመጣቸው፡

- ❖ በዕርዳታ የተገኙ በሆስፒታል አገልግሎት ላይ የሚውሉና አገልግሎት የማይሰጡ አልጋዎች በብዛት ተበታትነው መገኘታቸው፣
- ❖ በፌዴራል ሆስፒታሎች የመድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 001/2006 አንቀጽ 6.2 መሰረት ማንኛውም መድኃኒት ወደ ሆስፒታል ገቢ ሲደረግ የመድኃኒቱን የምርት መለያ ቁጥር፣ የማንነት መግለጫ፣ መጠን፣ የነጠላ ዋጋ፣ የውስጥ መለያ ኮድ እና የአገልግሎት ዘመኑን በሚገልጽ ለዚሁ አላማ ተብሎ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የታተመ የመድኃኒት የገቢ ደረሰኝ መሰረት በበጀት ምንጩ ተለይቶ መሆን እንዳለበት የተገለጸ፣ እንዲሁም ማንኛውም ሆስፒታል አግባብ ባለው ደረጃ እና የአምራቾች መስፈርት መሰረት መድኃኒቶችን እንደባህሪያቸው እና የበጀት ምንጫቸው ተለይተው በተገቢው ቦታ፣ የሙቀት መጠን፣ ጊዜ፣ የጸሀይ ጨረር እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ጥንቃቄዎችን በማሟላት መያዙን ማረጋገጥ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም በመቐለ ዩኒቨርስቲ የሪፈራል ሆስፒታል፡-
- ❖ የመድሐኒት ማስቀመጫ መጋዘን በሚመለከት ለመድኃኒትና ኬሚካሎች ለገቢ የሚጠቀሙበት ሰነድ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የታተመ የመድኃኒት የገቢ ደረሰኝ ቢሆንም በገቢ ደረሰኝና በቢን ካርዶች የበጀት ምንጩ እንደማይገለጽና በአንዳንድ መጋዘኖች በእርዳታ እና በበጀት የተገኙ መድኃኒቶች በግልጽ ተለይቶ አለመቀመጣቸው፣
- ❖ አንድ አንድ የመጠቀሚያ ጊዜ ማብቂያ ያልተጠቀሰባቸው ቢንካርዶች መኖራቸው፤
- ❖ የተለያየ መጠን ያላቸው ኦክስጅን ሪጉሌተሮች በአንድ ቢንካርድ መመዝገባቸው እና በአካል ቆጠራ ወቅት የኦክስጅን ሪጉሌተሮች ብዛት 174 የተገኘ ቢሆንም የቢንካርድ መጠን 257 በመሆኑ የልዩነቱ ምክንያት በወቅቱ ማስተካከያ በማድረግ ወጪውን የመመዝገብና ወቅታዊ የማድረግ ችግር መኖሩ፣

- ❖ በመመሪያው መሠረት ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ በየቀኑ የሰራቸውን በነጻ የሚታደሉ የመድኃኒት ማዘዣዎችን መዝግቦና በቅደም ተከተላቸው አደራጅቶ ለፋርማሲ አካውንታንት ማስረከብ እንዲሁም ማንኛውም የመድኃኒት ሂሳብ ባለሙያ በየቀኑ በነጻ የታደሉትን፣ በዱቤ እና እጅ በእጅ የተሸጡትን መድኃኒቶች ከመዝገቡ ላይ ለቅሞ የችርቻሮ እና አጠቃላይ ዋጋቸውን በማረጋገጥ ሪፖርት በሚቀርብለት አካል ስም በማደራጀት በነጻ፣ በዱቤና እጅ በእጅ ሽያጭ ስለታደሉት መድኃኒቶች ወርሃዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ቢኖርበትም ሪፖርቱ የሚቀርበው በየ3 ወሩ መሆኑ፣
- ❖ በመመሪያው መሠረት ማንኛውም ሆስፒታል በነጻ የሚታደሉ መድኃኒቶች ዝርዝርን የመድኃኒት ዕደላ በሚደረግበት ተገልጋዩ በግልጽ በሚያየው ቦታ ላይ በመለጠፍ ማሳወቅ ቢኖርባቸውም ይህ አሰራር እንደሌለ፣ በተጨማሪም በሽያጭ የሚቀርቡ መድኃኒቶች ዋጋቸው በዝርዝር በግልጽ መታየት እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ተገልጋዮች በሚያዩት መልኩ ዝርዝራቸውን በግልጽ በሚታይ መልኩ ወይንም በማሽጊያው ላይ ተጽፎ እንዳማይገኝ፣ተረጋግጧል፡፡

በ2007 በጀት አመት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች

- ❖ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር ለደመወዝ ሂሳብ ኦዲት በተወሰደ ናሙና መሠረት፣በ2007 በጀት አመት በዋናው ግቢ ለውጭ ሀገር መምህራን ከተከፈለው ደመወዝ ብር 1,647,835.55 ላይ ብር 552,229.94 የሥራ ግብር ተቀናሽ መደረግ ሲገባው ተቀናሽ ያልተደረገበት መሆኑ፣
- ❖ በዋናው ግቢ በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት ሂሳቦች መካከል ለ1 የውጪ ሀገር መምህር የታህሳስ/2007፣ የሚያዝያ/2007፣ የግንቦት/2007 እና የሰኔ/2007 ደመወዝና የቤት አበል በትምህርት ዝግጅታቸውና ማዕረጋቸው መሠረት ብር 311,906.73 (15,100 ዶላር) መከፈል ሲገባ ብር 398,662.25 (19,300 ዶላር) በመከፈሉ በብልጫ ብር 86,755.52 (4,200 ዶላር)የተከፈለ መሆኑ፣

- ❖ በትርፍ ሰአት ላስተማሩ መምህራን የተከፈላቸው ሂሳብ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ጠ.ሚ ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት መሆኑ ሲጣራ፡-በድምሩ ብር 610,372.00 ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
- ❖ ሚያዝያ 20/1990 በቁጥር 80-አጠ52/01/09 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተላለፈው መመሪያ መሠረት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ለትምህርት

  ወይም ሥልጠና ተልከው ትምህርታቸውን ስለሚከታተሉ ሠራተኞች የቤት አበል ጉዳይ ሳይጠቀስና ስለ ደመወዝ አከፋፈል ብቻ ተጠቅሶ እያለ በተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ በውጪ ሀገር በትምህርት ላይ ላሉ 15 መምህራን ለእያንዳንዳቸው በወር ከብር 800.00 እስከ ብር 1,000.00፣ በድምሩ ብር 26,800.00 በመመሪያ ያልተደገፈ የቤት አበል የተከፈላቸው መሆኑ፣
- ❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 38,739.00 የውሎ አበል ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
- ❖ የተማሪዎች ህብረት እስከ መጋቢት/2007 ከተለያዩ የውስጥ ገቢዎች ሰብስቦ ሲጠቀምበት የነበረ ሲሆን ከመጋቢት/2007 በፊት በህብረቱ የተሰበሰበው የገቢ መጠን ኦዲት ሳይደረግና ከወጪ ቀሪው ሳይታወቅ በባንክ እና በእጅ የነበረ በድምሩ ብር 529,361.20 ወደ ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ መደረጉ፣
- ❖ የመኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች እንደቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ በ2007 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት ባሉት የበጀት ዓመታት ርክክብ የተፈፀመባቸው ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- ❖ በኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣በተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ እና በቢዝነስ ኮሌጅ በከፍተኛ ገንዘብ ተገዝተው ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መወገድ ያለባቸው ማሽኖች በወርክ ሾፕ እና በተማሪዎች ምግብ ቤት ንብረቶች መኖራቸው፣
- ❖ ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ግንባታዎች ከኮንትራክተሮች ጋር በገባው ውል መሠረት ግንባታዎቹ ሳይጠናቀቁ ለዘገዩበት ዩኒቨርሲቲው ለደረሰበት ጉዳት /liquidation damage/ ከ5 ኮንትራክተሮች ማግኘት የሚገባው እስከ ዋናው ውል 10% ድረስ በየቀኑ የውሎቹ 1/1000ኛ (0.001) ተሰልቶ የ4 ግንባታ

ፕሮጀክቶች ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ብር 78,289,582.20 ላይ ብር 7,828,958.22 የጉዳት ካሳ ለመንግሥት ገቢ በዩኒቨርሲቲው የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ ድረስ የተሟላ እርምጃ አለመወሰዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ከሰላምታ ጋር</u>

<u>የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የመቐለ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመቐሌ ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በመቐሌ ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብን በተመለከተ</u>

1.1 <u>በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እና በሂሳብ ሪፖርቱ መካከል ስለታየው ልዩነት</u>

1.1.1.<u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/ሀ የሂሣብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት፤ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው በሚገልፀው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

በጤና ሣይንስ ኮሌጅ ብር 43,201.04፤ በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 19,208.74፤ በድምሩ ብር 62,409.04 /ከግል ሕክምና አገልግሎት የተገኘው ገቢ ሰኔ 30 በተደረገው ቆጠራ በገንዘብ ያዦች እጅ የተገኘ ሲሆን ዓመታዊ ሪፖርቱ ላይ የሚታይ ጥሬ ገንዘብ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

		የገንዘብ ያዥ ስም	የገቢው ዓይነት	በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረ	ዓመታዊ ሪፖርት የተደረገ
1	በጤናሳይንስ ኮሌጅ	በወ/ሮ ብርሃን ገብሩ	ከግል ሕክምና አገልግሎት	37,570.00	-
2		በርግአት አብርሃ	>> >>	5,631.04	-
3	ዓይደር ሆስፒታል	በቅዱሳን ክ/ጽዮን		3,699.74	-
4		አቶ አሸናፊ ሓለፎም	ከዕለት ገንዘብ ሰባሳቢ	15,509.00	-
	ድምር			62,409.04	

1.1.2 ስጋት

ሪፖርቱ የሂሳቡን ትክክለኛ ገጽታ ላያሣይ ይችላል ። ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት የተቆጠረው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ከጥሬ ገንዘብ የሌጀር ሚዛን የማይመሳከር ከሆነ በሚከሰተው ልዩነት ጉድለት ይሁን የምዝገባ ስህተት ለመሆኑ በቀላሉ ለማወቅ አያስችልም።

1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ለወደፊቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት በገንዘብ ያዥ እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ ሂሳብ ከጥሬ ገንዘብ የሌጀር ሚዛን ጋር ሊመሳከር ይገባል፡፡ልዩነቱም ተጣርቶ ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበ ሒሳብ ወደ መንግስት ባንክ በወቅቱ ገቢ ያልሆነበት ምክንያት በቀን 30/10/2009 ዓ/ም ለሊት ሙሉ ከፋርማሲ ክፍል፣ ከኢመርጀንሲ ሕክምና ክፍል፣ እንዲሁም ከካርድ ክፍል ከ24 የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበ መሆኑ ይታወቃል ፡፡ ሆኖም ግን የውስጥ ኦዲተሮችን ጥዋት በ1/11/2009 ዓ/ም መጥተው የሁሉም ካሸሮችን ካዝና ሰለ ታሸገ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ ሊሆን አልቻለም፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ ሁሉ ጊዜ በየዓመቱ የሚያጋጥመንና ለስራም ዕንቅፋት የሆነ ያለው ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሌ ለሊት የተሰበሰው ጠዋት ገቢ እንዳይሆን ካዝናው በኦዲተሮች በጥዋቱ 2፡ 00 ሰዓት ስለሚታሸግ ነው፡፡ ስለዚህ ያለንን ሁኔታ ግምት ውስጥ እንዲገባልን እንጠይቃለን፡፡

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ግኝት የሆነው በጥሬ ገንዘብ ተገኝቶ የተቆጠውና በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት መካከል ልዩነት አለ ይህም ልዩነት በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረው ብር 62,409.04 ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱ ግን ምንም አይነት የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ የለም የሚል ሲሆን በመውጫ ውይይቱ ወቅት ሰኔ 30 የዋለው አርብ ላይ መሆኑና የውስጥ ኦዲተሮቹ ደግሞ ሐምሌ 3 ቀን ቆጠራ ያደረጉ በመሆኑ በጊዜው የተቆጠረው ገንዘብ ቅዳሜና እሁድ (የሐምሌ አንድ እና የሐምሌ ሁለት) በመሆኑ ሪፖርቱ ላይ ሊታይ አለመቻሉን በውይይቱ ወቅት ሲገለፅ የተባለው ትክክል መሆኑን

ለማረጋገጥ የተሰበሰባቸውን ደረሰኞች እንዲቀርቡና በትክክል ገንዘቡ በዚያን ቀን ስለመሰብሰቡ መረጋገጥ እንዳለበት የተነጋገርን ቢሆንም ደረሰኞቹ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የተሰጠውን ምላሽ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለማስቻሉ ግኝቱ ባለበት ሆኖ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ሊስተካከል ይገባል፡፡

2. የገቢ ሂሳብ

2.1 በማነስ ሪፖርት የተደረገ የገቢ ሂሳብ

2.1.1.ግኝት

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/ሀ የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት፤ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 4 መሠረት መመሪያዎቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዓይደር ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ከግል ሕክምና አገልግሎት መስጫ ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ለገ/ኢ/ል/ት/ ሚ/ር ሪፖርት መደረግ የነበረበት ብር 82,224,535.69 ሲሆን ሪፖርት የተደረገው ብር 67,567,804.67 ብቻ በመሆኑ ልዩነት ብር 14,656,731.02 በማሳነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤
- ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ወጪ የተደረገው ብር 73,984,652,12 ሲሆን ለገ/ኢ/ል/ት/ ሚ/ር ሪፖርት የተደረገው ደግሞ ብር 65,097,129.44 በመሆኑ ብር 8,887,522.68 በማሳነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው	ሪፖርት መደረግ የነበረበት የገንዘብ መጠን	ሪፖርት የተደረገው የገንዘብ መጠን	ልዩነት/በማነስ ሪፖርት የተደረገው የገንዘብ መጠን/
ከተለያዩ የገቢ ምንጮች በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበ ገቢ	82,224,535.69	67,567,804.67	14,656,731.02
ከውስጥ ገቢ ወጪ የተደረገ ሂሳብ	73,984,652,12	65,097,129.44	8,887,522.68

2.1.2 ስጋት

የሂሳብ ሪፖርቱ የመ/ቤቱን ትክክለኛ ገጽታ ላያሳይ ይችላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ለሂሳቡ ተገቢው ማስተካከያ ተሰርቶለት ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በሚኒስትሮች ምክርቤት የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001 ተፈፃሚ ለማድረግ እንዲረዳ የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በመንግስት ሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የአሰራርና የአደረጃጀት መመርያ ቁጥር 001/2002 እና ይህንን አስመልክቶ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በድርጅቱ ሁለንትናዊ ቁጥጥር እንዲያደርር ስለሚፈቅድ ማንኛውም የፋይናንስ ቁጥጥር ወደ ኮሌጁና ሆስፒታሉ ሪፖርት እየተደረገ መሆኑን እየገለፅን ለቀጣይ ከውስጥ ገቢ ጋር በመደመር ወደ መንግስት ሪፖርት እንደምናደርግ እንገልፃለን!

2.2.1.ግኝት

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀፅ 5 ተራ ቁጥር 2/ሀ በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች ከዓመት ወደ ዓመት ቀጣይ ከሆኑና ሊታቀዱ ከሚችሉ ሥራዎች የሚገኘው የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የወጣው ወጪ በቦርድ መፈቀድ እንዳለበት በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል "ሀ" ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተገኘው የገቢ መጠን የገቢ ማስገኛ ሥራዎቹን ሙሉ ወጪ ሸፍኖ ተራፊው ገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአመታዊ የበጀት ጥያቄ ጋር አቅርበው የውስጥ ገቢው በመንግስት ሲታወጅ ለፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ይውላሉ፡፡ በዚህ መሰረት ተግባራዊ እንደሚደረግ ለማጣራት ኦዲት ስናከናዉን፡- ኮሌጁ ለተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ፈተና ለፈተነበት ከድርጅቶቹ ገቢ ያገኘ ሲሆን

- ❖ የተፈጥሮ ሳይንስና ቀመር ኮሌጅ ለመምህርንና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ብር 219,411.22 ለዩኒቨርሲቲው ብር 24,325..69 ገቢ የተደረገ መሆኑ፣
- ❖ የሕግና የሥነ -መንግሥት ኮሌጅ ለመምህርንና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ብር 43,701.60 ለዩኒቨርሲቲው ብር 4,570.40 ገቢ የተደረገ መሆኑ፣
- ❖ የቢዝነስና ኢኮኖሞክስ ኮሌጅ ለመምህርንና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ብር 93,015.00 ለዩኒቨርሲቲው ብር 15,483.00ገቢ የተደረገ መሆኑ፣

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ፈተና ለፈተኑበት ከድርጅቶቹ በአጠቃላይ ብር 400,506.91 ገቢ የተገኘ ሲሆን ለመምህራንና ለድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች 80% ብር 356,127.82 የተከፈለ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው 20% ብር 44,379.09 ገቢ እንዲሆን በዩኒቨርሲቲው ሴኔት በተወሰነው መሰረት የተፈፀመ እና የተገኘ ገቢ ለመምህራኑና የመንግስት ድርሻ የክፍፍሉ መጠን (Rate) በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይወሰንና ክፍፍሉም በቦርድ ሳይጸድቅ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡

2.2.2 ስጋት፡-

አሰራሩ መመሪያን ያልተደገፈ መሆኑ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ኮሌጁ የሚያገኘውን ገቢ (ትርፍ) ፍትሃዊ በሆነ ክፍፍል መከናወን ይኖርበታል፡፡

2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

እስከ አሁን ድረስ ስንሰራበት የቆየነው ድርጅቱ ከዩኒቨርሲቲያችን ጋር በገባው ውል መሰረት ሲሆን በውሉ መሰረትም ክፍያ ስንፈጽም ቆይተናል። ስህተት መሆኑ ከተገለጸልን ግን በሚመለከተው አካል በማስፈቀድ እንሰራበታልን። በማለት ገልፀዋል፡፡

2.3 ያልተሰበሰበ ገቢ

2.3.1. ግኝት

ዩኒቨርሲቲው በሥራ እንቅስቃሴው የሚሰበስባቸው ገቢዎች የመንግስት ደንብና መመሪያን ተከትሎ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ❖ በሪፈራል ሆስፒታል የዱቤ ህክምና አገልግሎት ውል ከገቡ ተቋማት አገልግሎት ላገኙበት ክፍያ ብር 1,120,001.90 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- ❖ ከንግድ ቤቶች በበጀት ዓመቱ መሰብሰብ የነበረበት ብር 558,473.54 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- ❖ በዓይደር እና በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከንግድ ቤቶቹ ብር 2,393,188.37 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ የሚታይ ሲሆን ስለመሰብሰቡ ለማጣራት ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፡

- ከ2005 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ዓመት ድረስ ያልተሰበሰበ ከ 3 ተከራዮች (ግርማይ በርሀ የልብስ ሰፌት፤ ፀጋ ገ/ስላሴ /ጃምቦ/ ካፌና ሬስቶራንት እና ሙሉ ብርሃነ ካፌና ሬስቶራንት) ስለሚፈለገው የገቢ ሂሳብ ብር 1,982,522.30 ጉዳዩ ለህግ ክፍል የተመራ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ምንም እርምጃ ሳይወሰድ የሚገኝ ሲሆን

በጠቅላላው ብር 6,054,186.11 ውዝፍ የገቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

2.3.3 ስጋት፤

በውሉ መሠረት መሰብሰብ የሚገባው ገቢ በወቅቱ አለመሰብሰብ መንግስት በዕቅድ በያዛቸው ሥራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይሰበሰብበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.3.4 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ሆስፒታሉ በተገቢው ውለታ መሠረት ከህክምና እና ከኪራይ አገልግሎት የሚገኘው ገቢ በወቅቱ ያልተሰበሰበበት ምክንያት ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ በሌሎቹም በዱቤ ህክምና ላይ በሚታዩ የአሠራርና የውስጥ ቁጥጥር ግድፈቶች ላይ የሥራ አመራሩ የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሆኔታ እንዳይከሰት የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.3.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- እስከ አሁን ድረስ ክፍያቸውን ያጠናቀቁ ወደ ዩኒቨርሲቲው የባንክ አካውንት ገቢ ስለሚያደርጉ ደረሰኛቸው እያሰባሰብን ሲሆን ክፍያ መፈፀም ያልቻሉት ደግሞ ጉዳያቸው በዩኒቨርሲቲው ህግ ክፍል እንዲታይ እየተደረገ ነው፡፡

- ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርነው ክፍያ ወደ ዩኒቨርሲቲው የባንክ አካውንት ገቢ ስለሚያደርጉና ደረሰኛቸውም ለፋይናንስ ስለሚሰጧቸው ለክትትል ተቸግረን ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የሁለትና የሦስት ወር አንድ ላይ ሰብስበው ያስገቡት ገንዘብ ነው በ2010 በጀት ዓመት ገቢ ተደርጓል የተባለው፡፡ ከዚህ በኃላ ግን በተቻለን መጠን

ቁጥጥር በማድረግ በወቅቱ ገቢ እንዲያደርጉ ክትትል የሚደረግ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

❖ በዓይደር ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚታከሙ የዱቤ ታካሚዎች ከክልል ትግራይ ጤና ቢሮ የሚከፈል በክልሉ የሚኖሩ ከፍለው መታከም የማይችሉ እና በጤና መድህን ፕሮግራም ላልታቀፉ ዜጎች የዱቤ አገልግሎት እንድንሰጥለት እና ክፍያውም በየሦስት ወር እንዲከፈል ውል በገባው መሰረት የተፈፀመ ሲሆን በተደጋጋሚ ለክልል ጤና ቢሮ የክፍያ ጥያቄ ቢቀርብም በቢሮው በጀት እጥረት ምክንያት እስከ አሁን ክፍያውን ሊፈፅምልን አልቻለም ፡፡

❖ በጤና ሳይነስ ኮለጅ የሚገኙ የንግድ ድርጅቶች የቤት ክራይ በተመለከተ ከሚያዝያ 2008 ዓ/ም ጀምሮ በድጋፍ ሰጭ ምክትል ፕሬዚዳንት በኩል ማንኛውም የንግድ ድርጅት በሆስፒታሉ የሚገኙ የቤት ኪራይ ወደ ዩኒቨርስቲ ገቢ ማመንጫ ስር እንዲተዳደሩ ስለ ተወሰነ ከውሳኔው በፊት የነበረው ግን መሰብሰቡን እንገልፃለን ፡፡ አባሪም አያይዘናል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው የወጪ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት ታምኖበት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1.1 <u>ደመወዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች፤</u>

3.1.2 <u>የክፍያ ተመን ሳይኖረው የተፈፀመ ክፍያ</u>

3.1.3 <u>ግኝት</u>

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 13/2003 በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበለትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ ክፍያ የሚፈፀም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ለኤግዛማይነር ክፍያ

❖ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 369,280.00

❖ የተፈጥሮ ሳይንስና ቀመር ኮሌጅ ከመደበኛ በጀት ብር 336,000.00

❖ የህብረተሳብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 1,705,000.00

- ❖ የእንስሳት ሳይንስ ሕክምና ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 186,700.00
- ❖ የሕግና የሥነ -መንግሥት ኮሌጅ ከመደበኛ በጀት ብር 321,000.00
- ❖ የቢዝነስና ኢኮኖሞክስ ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 161,500.00
- ❖ የህፀተ ዝናብና ግብርና ኮሌጅ ብር 91,800.00

በድምሩ ብር 3,171,280.00 ተመን ሳይኖረው የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

ከመመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

3.2.3. የማሻሻያ ሀሳብ

ዩኒቨርሲቲው ማንኛውንም ክፍያ መንግስት ባወጣው መመርያና ደንብ ብቻ መክፈል ያለበት ሲሆን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ክፍያዎች እንዳይፈፀሙ ጥብቅ ክትትል መደረግ አለበት፡፡ እንዲሁም ክፍያው ተገቢነት ካለው ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሲፈቀድ ብቻ ሊከፈል ይገባል፡፡

3.2.4. የስራ አመራሩ ምላሽ፣

እስከ አሁን ድረስ በትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የጸረቀ የአከፋፈል ተመን ስላልወጣለትና በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰራበት በመሆኑ ስንከፍል ቆይተናል። ሆኖም ዩኒቨርሲቲው ለትምህርት ሚኒስቴርና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀርብን ሲሆን እስከ አሁን ድርስ ምንም ምላሽ አልተሰጠንም። የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዳይስናከል ግን አሁንም ጥያቄያችን ለሚመለከተው አካል እናቀርባለን። በማለት ገልፀዋል፡፡

3.3 አላግባብ የተከፈለ

3.3.1 ግኝት

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ‹‹ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና

ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ እንዳሳሰበ›› መመሪያው ቢያመለክትም፤

- በኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የAdhoc ኮሚቴ በሚል ብር 39,000.00፤
- በህግና ስነ-መንግስት ኮሌጅ የኮሚቴ ክፍያ በሚል ብር 52,400.00፤

በጠቅላላው ድምር ብር 91,400.00 አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በአባሪ ቁ.4 ተመልክቷል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

ክፍያው መመሪያውን መጣሱ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ከመዳረጉም ባሻገር የመንግስት መመሪያዎች እና ደንቦች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ በማድረግ ለሌሎች ብልሹ አሰራሮች በር ሊከፍት ይችላል ፡፡

3.2.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

አላግባብ ከመመሪያ ውጪ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

3.2.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**

የኮሚቴውን ክፍያ በተመለከተ መምህራን ክምሆናችዉ አንጻርና ስራዉም በትርፍ ጊዜ የሚሰራ በመሆኑ ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ሚ/ር በተፈቀደልን መሰረት የትርፍ ሰአት ክፍያዉን ፈጽምናል።

3.1.2 **ለውጭ ሀገር መምህራን ከተመን በላይ የተከፈለ ደመወዝ**

3.1.3 **ግኝት**

የውጪ መምህራን የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ጥቅምት 2001 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2.2.12 የተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በሚለው ስር ‹‹የውጭ መምህራን ያላቸውን ሙያና የአካዳሚክ ደረጃ መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባውን የደመወዝ መጠን በተመለከተ በመደራደር ይወሰናል፡፡ ይህ የደመወዝ መጠን በትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክና ደረጃ ከተቀመጠው ጣሪያ (Scale) በላይ መሆን እንደሌለበት›› መመሪያው ቢያመለክትም፤

በዋና ግቢ

- ዩኒቨርሲቲው ለውጭ አገር መምህራን ባላቸው የሙያና የአካዳሚክ ደረጃ መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባውን የደመወዝ መጠን ትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክና

ደረጃ ካስቀመጠው ጣሪያ (Scale) በላይ ለ16 መምህራን በድምሩ $ 37,590.00 ክፍያ የተፈፀመ የደመወዝ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁ 6 ተመልክቷል፡

3.3.2. ስጋት

ከመመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡

3.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ከመመሪያ ውጪ አላግባብ ለውጭ አገር መምህራን የተከፈለው የደመወዝ ሂሳብ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የውጪ አገር መምህራን ደመወዝ ክፍያ ባላቸው ሙያና የአካዳሚክ ደረጃ በተቀመጠው ጣሪያ (Scale) መሰረት ብቻ እንዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

3.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሁለት የውጭ ዜግነት ያላቸው ባለሞያዎች በተለያዩ የስራ ዘርፍና የመማር ማስተማር ሂደት የሚያግዙን በመሆናች ከስኬል ውጭ ሲከፈላቸው ቆይቷል፡፡ በመሆኑም አንዱ የሱዳን ዜጋ ውሉ ተቋርጦ ወደ አገሩ ሄደዋል፡፡ ሌላው ባለሙያ ግን ክፍያው ስህተት መሆኑን ተገንዝበን ማስተካከያ የምናደርግ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ በማለት በምላሻቸው ላይ ገልፀዋል፡፡

3.4. የውጪ ሀገር መምህራንን የሥራ ግብር በተመለከተ

3.4.1. ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 4 ማንኛውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚገኘው ጠቅላላ የወር ገቢ ላይ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት ግብር መክፈል እንዳለበት እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸ ቢሆንም፤

- ❖ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጪ ሀገር መምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ16 የውጪ ሀገር መምህራን የደመወዝ ክፍያ ሲፈፀም የሥራ ግብር ብር 1,042,683.10 መቀነስ እያለበት ሳይቀነስ የተከፈለ መሆኑ፣
- ❖ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ከፈረንሳይ እና ከህንድ ለሚመጡ መምህራን የማስተማር /የምርምር አገልግሎት ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ቀን አንስቶ ከሁለት አመታት ላልበለጠ ጊዜ ከግብር ነፃ መሆናቸውን መመሪያው ቢያመለክትም፤ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ የተቀጠሩ የህንድ ሀገር መምህራን ከግብር ነፃ የሚሆኑበት የጊዜ ገደብ ካለቀ በኃላ ለ39 የህንድ መምህራን የሥራ ግብር ከ7 ወርእስከ 9 ዓመት ባለው ጊዜ መክፍል ያለባቸውን የሥራ ግብር ያልከፈሉ ሲሆን በናሙና ከታየው ውስጥ የግንቦት እና የሰኔ/2009 ብር 4,115,511.65 የተከፈላቸው ቢሆንም የሥራ ግብር ብር 1,323,429.08 መቀነስ እያለበት ሳይቀነስ የተከፈለ መሆኑ፣

በጠቅላላው ብር 2,366,112.18 ያልተቀነሰ የሥራ ግብር መኖሩ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 7 ተመልክቷል፤

3.4.2. ስጋት

በመንግሥት ደንቦች እና መመሪያዎች ተፈጻሚ አለመሆን የመንግስት ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅም እንዲውል መንገድ ከመክፈቱም በተጨማሪ መንግስት በበጀት ዓመቱ ሊገኝ የሚችለውን ገቢ ያሳጣል፡፡

3.4.3. የማሻሻያ ሀሳብ

በመንግስት ደንብ እና መመሪያ መሠረት የሥራ ግብር መሰብሰብ ወይም ከግብር ነፃ ለመሆናቸው ማስረጃ ሊኖር ይገባል፡፡ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጣውን መመሪያ ማገናዘብ ይገባል፡፡ አላግባብ የሥራ ግብር ሳይቀነስ የተከፈለው ክፍያ የመንግስትን ገቢ የሚያሳጣ ስለሆነ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጪ ሀገር መምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከግብር ነፃ አለመሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩት ደግሞ ቅጥራቸው አልቆ ወደ አገራቸው

ተመልሰው እንደገና ስለሚቀጠሩ አዲስ ቅጥር ናቸው በማለት የስራ ግብር አልቆረጥንም፡፡ ስህተት መሆኑ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ግን አስፈላጊውን ግብር እየቆረጥን መሆኑን እንግልጻለን፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

3.6 በሀገር ውስጥ እና በውጪ ሀገር ትምህርታቸውን ተከታትለው ያልተመለሱና የውል ግዴታቸውን ያልተወጡ መምህራኖችን ሂሳብ በተመለከተ

3.6.1.ግኝት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና አፈፃፀም በመስከረም/2004 ዓ.ም ላይ በክፍል ሰባት በአንቀፃ 7.2 በንፅስ አንቀፃ 7.1.8 ለማስተር ድግሪ ከሃያ አራት ወር (2 ዓመት) ለዶክትሬት ድግሪ ከአራት ዓመት መብለጥ እንደሌለበት ከበለጠ ግን እድሉን የሰጠው ተቋም ማረጋገጥ አንዳለበት›› በሚያመለክተው መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በዋናው ግቢ

በዩኒቨርሲቲው በሀገር ወስጥ እና ከሀገር ወጭ ውል ገብተው ለት/ት ወደ ውጪ ሀገር ከተላኩት መምህራን መካከል ለሁለተኛ ዲግሪ 9 ለሦስተኛ ዲግሪ 22 በድምሩ 31መምህራን ከላይ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመለሱ ሲሆን አካዳሚክ ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ሳይቀርብ በበጀት ዓመቱ ብር 499,693.50 የደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ወጪ ሆኖ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 9 ተመልክቷል፡፡

3.6.2. ስጋት

ጊዜያቸውን ጨርሰው የማይመጡ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የተቋሙን እቅድ ለማሳካት እና የመምህርን እጥረት ለመቀነስ ካለማስቻሉም በተጨማሪም መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ መንገድ የሚከፍት አሰራር ነው፡፡ መመሪያውን ያልተከተለ አሰራር ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

3.6.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ውጪ አገር እና ሀገር ውስጥ የትምህርት ዕድል አግኝተው ለሚማሩ አካዳሚክ ባለሙያዎች በወቅቱ ያልተመለሱ መምህራን ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው

ምክንያቱ ተጠቅሶ ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

3.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- ❖ ለክሱ መዘግየት ምክንያት የሚከሰሱት ሰራተኞች አንፃር ብዛት በመኖሩ በደብዳቤ በመጣበት ሳይሆን በቅርብ የሚገኙና ሊፈፅሙ የሚችሉትን ቅድሚያ በመስጠት እየተከፋፈለ ክስ ስለሚመሰረት፤
- ❖ በዝርዝሩ ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ዋስና ውል ተቀባይ አድራሻቸው የማይታወቅ፣ እርሰበርስ ተዋውሰው የጠፉ ሆነው ጉዳዩ ግን ለክስ የሚሆን መረጃ በማሰባሰብ ላይ መሆኑን፤
- ❖ የተቀመጠው ገንዘብ መጠኑ ከተቀመጠው ሊያንስ ይችላል ምክንያቱም መጥተው የተወሰነ አገልግለው የጠፉም ስለሚኖሩ፤
- ❖ የሰው ሃይል እጥረት በፅ/ቤቱ አለ ----ደብዳቤዎች ለክስ ከመጡ በኋላ በት/ት የቆዩ ሰራተኞች በት/ት ሁኔታ ምክንያት፣ ዘግይተው የመምጣት ሁኔታ ይኖራልና የተመለሱም ሊኖሩ ይችላሉ። እንዲሁም በፍላጎት ከክስ በፊት የሚከፍሉ አሉ።

እነዚህ ከላይ ስማቸው የተዘረዘሩት ያልተከሰሱት ብቻ ስለተጠየቅን እንጂ በክስም ከክስ በፊት እንዲከፍሉ እናደርጋለን ለምሳሌ ያክል በ2009 ዓ/ም 795,423.48 በ2010 ዓ/ም እስካሁን ባለው 1,033,197.67 በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ያልተወጡ ሰራተኞች አስከፍለን ወደ መንግስት ካዝና እንዲገባ አድርገናል። በማለት ገልፀዋል።

3.8. ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያልሆነ የጉዳት ካሳ

3.8.1.ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሽ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሽ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል

መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በዚህ መሠረት ለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ የህንፃ ስራው ለዘገየበት ከ 2 የስራ ተቋራጮች ላይ በዋናው ግቢ መሰብሰብ የነበረበትና ያልተሰበሰበ ብር 527,041.04 ከተለያዩ የእቃ አቅራቢዎች በወቅቱ እቃውን ገቢ ባለማድረጋቸው ብር 3,395,373.68 በጠቅላላው ብር 3,922,414.72 መክፈል የሚገባቸው የጉዳት ካሳ ያልከፈሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

1	በዋናው ግቢ (ከግንባታ)	527,041.04
	ከእቃ አቅራቢዎች	
	ዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል	634,541.67
	በጤና ሳይንስ ኮሌጅ	65,993.40
	በቴክኖሎጂ ኢንስትትዩት	2,693,348.21
	የህብረተሳብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ	1,490.40
	በድምሩ	3,922,414.72

3.8.2. ስጋት

- ሊያገኝ ያቀደውን አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥርበታል፡፡
- አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በጨረታ ያሸነፉትን ንብረት ገቢ እንዲያደርጉ ካልተደረገ ዩኒቨርሲቲው ከገዛው ዕቃ ሊያገኝ ያቀደውን አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥርበታል፡፡

3.8.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ዩኒቨርሲቲው ከላይ የተመለከተውን ከኮንትራክተሮቹ እና አቅራቢዎቹ እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በገቡት ውል መሠረት አገልግሎቱን ካልሰጡ በመመሪያው መሠረት መክፈል ያለባቸውን የጉዳት ካሳ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡

3.8.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- MUBP-105፤- ላልተጠናቀቀ ቀሪ ስራ የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ውል 10% የባንክ ዋስትና (unconditional bank Guarantee) በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት አሰርቶ ማቅረቡና ፣ ቀሪው ስራ ለማጠናቀቅ በመስራት ላይ መሆኑን፤
- MUBP-107፤- ላልተጠናቀቀ ቀሪ ስራ የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ውል 20% ዋስትና ከታወቀ ባንክ አሰርቶ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ተሰጥዋል ፣ ቀሪው ስራ ለማጠናቀቅ በመስራት ላይ መሆኑን፤

3.9 የገቢ ደረሰኝ (RV)ያልተቆረጠለት ገቢን በተመለከተ

3.9.1 ግኝት

በመመሪያው መሠረት ገቢ ለተደረጉ ገቢዎች የገቢ ደረሰኝ በአግባቡ ለመቆረጡ ኦዲት ሲደረግ፤የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 22 ን.አንቀጽ 2 ገንዘብ ለመሰብሰብ ውክልና የተሰጠው ሰው ለሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ህጋዊ የገቢ ደረሰኝ ለከፋዩ መስጠት እንዳለበት መመሪያው ቢያመለክትም በመመሪያው መሰረት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በውሉ መሰረት አቅራቢዎቹ ዕቃውን አጠናቀው ገቢ ማድረግ ባለባቸው ቀኖች ስላላስገቡ ላዘገዩበት ከድርጅቶቹ የተቀነሰው ከዋናው ግቢ ብር 1,236.61፤ ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 337,408.28 በድምሩ ብር 338,644.89 የጉዳት ካሳ ተቀንሶ በ1489 ሂሳብ መደብ ላይ የተመዘገበ ቢሆንም የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ ታውቋል፡፡

3.9.2 ስጋት

ያልተሰበሰበን ገንዘብ እንደተሰበሰ ተደርጎ ምዝገባው ሊከናወን ይችላል፡፡ ገንዘቡን ለከፈለው አካል ስለመክፈሉ ማስረጃ እንዳይኖረው ከማድረጉ በላይ በድጋሚ እንዲከፍል ሊጠየቅ ይችላል፡፡

3.9.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ገቢ ለቁጥጥርና ክትትል አመች ባለመሆኑ፣ዩኒቨርሲቲው ከጉዳት ካሳ ያገኘውን ገቢ ተገቢው የገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት ለወደፊቱም የሚመለከተው የሥራ ክፍል ተገቢውን ግንዛቤ ሊያደርግ ይገባል፡፡

3.9.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በክፍያ ማዘዣ ክፍያ በምንፈፅምበት ወቅት ቆርጠን ያስቀረን ሲሆን ደረሰኝ ግን አልቆረጥንለትም ነበር አሁን ግን ማስተካከያ እያደረግን ነው፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

3.11.2 ግዥን ቆራርጦ መግዛት

3.12.1. ግኝት

ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንጽ 2 በአዋጅና በመመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 24.12 ላይ ደግሞ ለፕሮፎርማ ግዥ በተፈቀደው አንቀጽ ግዥ ለመፈጸም ሲባል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ

22.በዋናው ግቢ ብር 700,150.72

23.በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 797,527.92

የዩኒቨርሲቲው የግዥ ክፍል የመንግስትን ወጪ ሊቀንስ በሚችል መልኩ የግዥ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ አውጥቶ በርካታ ድርጅቶችን በማሳተፍ የመንግስት ጥቅም ማስጠበቅ ሲገባ፣ በናሙና ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ፣ ግዥን በመቆራረጥ የተከናወኑ ክፍያዎች ብር 1,497,678.64 ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3.12.2. ስጋት፣

ከተፈቀደው የግዢ ስርዓት ወጪ ግዢ መፈጸም ግዢዎች ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለዉ ጥቅም እንዳያስገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.12.3. የማሻሻያ ሀሳብ

የግዥ ፍላጎትን በአንድ አሰባስቦ ግዥ ማከናወን ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ለማግኘት እንዲቻል የዕቃና አገልግሎት ግዢዎች በመንግስት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪዎች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በግዢ ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

3.12..4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ

በዋናው ግቢ እና በእንስሳት ህክምና ኮሌጅ ተቆራርጦ የተተፈፀመ ግዥ ተብሎ ለቀረበው ግኝት ምንም እንኳን ተመሳሳይነት ያላቸው እቃዎች ቢሆንም የተጠቀሷ የገንዘብ መጠን በፕሮፎርማ የሚካተት መጠን መሆኑ እንዲሁም ግዥው የተፈፀመበት ወቅት የተለያየ መሆኑና ግዥው የተፈፀመው ሆን ተብሎ ተቆራርጦ እንዲፈፀም ያልተደራገ መሆኑ

እያረጋገጥን ነገር ግን አስተያየቱን በመቀበል ተመሳሳይነት ያላቸው ግዝዎች በተደራጀ መልክ በግልፅ ጨረታ ግዥ እንዲፈፀም የሚደረገው ጥረት ከግዜ ወደ ግዜ እየተጠነከረ በመሆኑ አስተያየቱን በመቀበል ለወደፊቱ እንዲስተካከል የምናደርግ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

3.14 እቃው ስለመግባቱ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠ ስለመሆኑ፤

3.14.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመርያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፤ ንዑስ አንቀጽ 3 ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወደ መስሪያ ቤቱ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት ተገልጿል፤፤ይሁን እንጂ

- የእንስሳት ህክምና ኮሌጅ በቀን13/01/09 በቫውቸር ቁጥር 714561 ለእንስሳት መኖ የሚውል የሳር ክምር ከአበርገለም አለም አቀፍ የእንስሳት ሃብት ልማት በብር 137,662.99 ግዥ ያከናውነ ቢሆንም ዕቃው በሞ/19 ገቢ ሳይሆን ክፍያ መፈፀሙ፤
- በህግና ስነ-መንግስት ኮሌጅ በቀን 14/10/09 በደረሰኝ ቁጥር 0875875 ለ5ኛ አመት ለህግ ተመራቂ ተማሪዎች በብር 12,000 የመጽሄት ግዥ ያከናወነ ሲሆን መጽሄቱ በሞ/19 ገቢ ሳይሆን ክፍያ መፈፀሙ፤

በድምሩ ብር 149,662.99 በሞ/19 ገቢ ሳይሆን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

3.14.2 ስጋት

የተገዘው ዕቃ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይሆን ክፍያ ከተፈጸመ የመንግስት ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.14.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ማንኛውም ክፍያ ሲከናወን የተገዙ ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ስለመሆናቸው ተረጋግጦ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡ ስለዚህ ገቢ ባልሆነ ዕቃ ለተፈጸመው ክፍያ ተጣርቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.14.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በእንስሳት ህክምና ኮሌጅ በህግና ስነ መንግስ ኮሌጅ እቃው ሰለመግባቱ የሚያሳይ ማስርጃ ሞዴል 19 ሳይኖር ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝተዋል ተብሎ ለቀረበው ግኝት በአገልግሎት ወይም በግንባታ ስራ ተሳቢ ተደርጎ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በእቃነት የሚመደብ ግዥ በሞዴል 19 ገቢ ተደርጎ ክፍያ መፈፀም እንዳለበት

ይተመናል በመሆኑም ይህንን ሁኔታ በዚህ መልክ እንዲስተካከል የሚደረግ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት በመነጋገር እንደሚስተካከል፤

3.15. በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝና በተራ ፋክቱር የተወራረደ ሂሳብ፤

3.15.1 የዱቤ ሽያጭን በተመለከተ

3.15.2 ግኝት

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው፤

- ❖ በዋናው ግቢ በቀን 24/9/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 178165 በሂሳብ መደብ 6211 ከአንበሳ ጫማ አክስዮን ማህበር ጫማ ለተገዛበት ብር 912,775.86 ሲከፈል መቅረብ ያለበት የሽያጭ ደረሰኝ (cash sale invoice) መሆን ሲገባው፣ እንደ ሽያጭ ደረሰኝ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (Cerdit sale invoice) ቀርቦ ሂሳቡ የተወራረደ መሆኑ፤
- ❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የቢሮ እቃዎች መደርደሪያ ሸልፍ ለመግዛት በ11/11/08 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 446377 ለሙሉ ክብሮም ዛፉ የቢሮና የቤት እቃዎች አቅራቢ ለተከፈለ ብር 891,809.75 የሽያጭ ደረሰኝ ሳይቀርብ በAttachement Cash Sales invoice ብቻ ሂሳቡ የተወራረደ መሆኑ፤

3.15.3 ስጋት

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ግዥ ሲያከናውን ዋናውን ደረሰኝ ካልተቀበለ መንግስት ከአቅራቢው ዓመታዊ ትርፍ ላይ ማግኘት ያለበትን የታክስ ሊያጣ ይችላል፡፡

3.15.4 የማሻሻያ ሀሳብ

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ክፍያ ሲከናወን ለግዥም ሆነ ለአገልግሎት ለተከፈለበት ሂሳብ ሲወራረድ የሽያጭ ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡ በመሆኑም ከድርጅቶቹ የሽያጭ ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.15.5 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ ምላሽ አልሰጠም

3.16 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ

3.16.1 ግኝት

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ❖ ዋና ግቢ ብር 13,660,905.78
- ❖ የዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 7,943,271.52
- ❖ የተፈጥሮ ሳይንስና ቀመር ኮሌጅ ብር 122,940.00
- ❖ የህብረተሳብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ ብር 1,869,559.95
- ❖ የሕግና የሥነ -መንግሥት ኮሌጅ ብር 17,726.23

በድምሩ ብር 23,616,403.48 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ ገንዘቡ ተከፍሎ እና ሂሳቡ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 17 ተመልክቷል

3.16.2 ስጋት

ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ በፈፀመበት እና አቅርቦቱን ባገኘበት በጀት ዓመት ሂሳቡ በወጪ ባለመመዝገቡ የበጀት አጠቃቀሙን የተዛባ ያደርገዋል፤በተጨማሪም አላግባብ መንግስትን ለድጋሚ ወጪ የሚጋብዝ አሰራር ከመሆኑም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

3.16.3. የማሻሻያ ሀሳብ

በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች ማከናወኛ ከተፈቀደለት በጀት የቀድሞውን በጀት ዓመት ክፍያ መፈጸሙ ተቋሙ የበጀት ህጉን ተከትሎ አለማከናወኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ እና ተገቢው የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል ፡፡

3.16.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በበጀት እጥረት ምክንያት በበጀት ዓመቱ ሳይከፈል የተላለፈና ግዥዎቹና ክፍያዎቹ ለዩኒቨርሲቲው በጣም አስፈላጊ ለዩኒቨርሲቲው ተከታታይ ስራ ግብአት

የሆኑ ክፍያዎች ሲሆኑ በተከታይ በጀት ዓመቱ በጀት የተያዘለት መሆኑን በማረጋገጥ የተከፈለ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡ ክፍያዎቹም አስፈላጊ ከመሆናቸው አንፃር በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ኮሚቴ እንዲወሰን በማድረግ ነው፡፡

3.17 የሂሣብ አርዕስቱን ሳይጠብቅ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

3.17.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት ለመከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፡

- ዋና ግቢ ብር 2,173,916.00
- የዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 2,645,239.09
- ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 124,680.00
- መቐለ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 364,353.62
- የእንስሳት ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 322,408.04

በድምሩ ብር 5,630,596.75 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

3.17.2 ስጋት፤

ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ አርዕስት ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

3.17.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያደርስ በመሆኑ ወጪዎች የሚመዘገቡት በትክክለኛው የበጀት አርዕስታቸው ለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.17.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ ምላሽ አልሰጠም፡፡

3.18 በቅድሚያ ሂሳብ የተሰጠን ገንዘብ ከክፍያ ላይ ያለመቀነስ

3.18.1 ግኝት

ዩኒቨርሲቲው በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የሰጣቸውን ክፍያዎች በወቅቱ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲና ቅድስትና መስፍን ደረቅ እንጀራ መጋገርና ማቅረብ ሕ/ሽ/ማህበር ጋር እንጀራ ለመጋገር በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት ውል ያሰሩት ከመስከረም 21/08 - ሰኔ 30/08 ሲሆን አቅራቢዎቹ በቀን 30/12/08 እና 13/01/09 በማመልከቻ ቅድሚያ ክፍያ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት ተፈቅዶላቸው በደረሰኝ ቁጥር 289440 ብር 27,147.71 እና በደረሰኝ ቁጥር 289452 ብር 38,457.76 የወሰዱ ቢሆንም ከቀጣይ ክፍያ ላይ በቅድሚያ የወሰዱት ብር 65,605.47 መቀነስ ሲገባው ሳይቀነስ ብር 143,415.00 ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፤ እንዲሁም ቅድሚያ ክፍያው ሲፈቀድላቸው ውል ያላደሱ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.18.2 ስጋት

- የአቅራቢዎቹ በስራው የመቀጠል ሁኔታ ሳይረጋገጥና ምንም አይነት መያዣ (መጠየቂያ) ሳይኖር ቅድሚያ ክፍያ መስጠት ገንዘቡን ተመላሽ ላይሆን ይችላል፡፡
- በቅድሚያ ክፍያ የተወሰደ ገንዘብ ባለመቀነሱ ምክንያት ገንዘቡ እንዲባክንና እንዲመዘበር ያደርገዋል፡

3.18.3 የማሻሻያ ሃሳብ

- ቅድሚያ ክፍያ የሚሰጠው የስራው ቀጣይነት ሲረጋገጥና ተጠያቂነት ሲኖረው መሆን አለበት፤
- ዩኒቨርስቲው ማናቸውም ቅድሚያ ክፍያ ወይም ተሰብሳቢ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት ባደረገ መልክ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

3.18.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለባለጉዳዮቹ ተነግሯቸዋል ማህበር እንደመሆናቸው መጠን ተሰብስበው እስኪወስኑ ድረስ የተወሰነ ቀናት እንዲሰጣቸው ስለጠየቁን በቅርብ ቀናት ውስጥ እናስመልሳቸዋለን፡፡ በማለት ገልፀዋል››

3.19 የሕንጻና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተመለከተ

3.19.1.ግኝት ለግንባታ ሥራ ዘርፍ አላግባብ ስለተደረገ የዋጋ ጭማሪ

በፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 5 አንቀጽ 25 .3 መሠረት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን በቴክኒክ ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ከመጀመሪያው ውል ተነጥለው ሊሰሩ የማይችሉ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎችን ግንባታውን እያከናወነ ከሚገኘው ሥራ ተቋራጭ መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት ከመጀመሪያው ውል ጋር ሲነፃፀር ከ30% የማይበልጥ ተጨማሪ የግንባታ ሥራ ማሠራት እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በዋናው ግቢ በኤ.ቲ.ኤስ ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግል ማ.የካፍቴሪያ ብሎክ የቫውቸር ቁጥር 0717927 በቀን 06/06/09 ከመጀመሪያው የውል ጠቅላላ ዋጋ ብር 10,885,260.37 ብር 3,265,578.11 የዋጋ ጭማሪ ማድረግ ሲገባ ብር 5,570,358.16 ተጨማሪው የግንባታ ሥራ እንዲሰራ በመደረጉ አላግባብ ብር 2,304,780.05 የዋጋ ጭማሪ ተደረጎና ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.19.2. ስጋት

በመንግሥት ታምኖባቸው የወጡ ህጎች፣ደንቦች፣የአፈፃፀም መመሪያዎች ተፈፃሚ ላይሆኑ ይችላሉ፡

3.19.3. የማሻሻያ ሀሳብ

በህግ በደንብ እና በመመሪያ መሠረት ክፍያዎች ማከናወን ይገባል፡፡

3.19.4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፣

ዩኒቨርሲቲያችን ካፍቴሪያው በ2003 ዓ.ም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ለመቀበልና ለማስተናገድ ከሥራ ተቋራጩ ውል የታሰረበት የG+0 ካፍቴሪያ ወደ G+1 እንዲቀየርና የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በተቀጽላ ውል ሥራው ተከናውኗል፡፡

4.1.የተሠብሣቢ ሂሳብ፤

4.1.1.ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ

ከተመለሰ በኂላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና የዩኒቨርስቲው የተሰብሳቢ ሂሳቦች በደንቡና በመመሪያው መሰረት እንዲወራረዱ የሚደረግ መሆኑ ሲጣራ፤ ከመደበኛ በጀት ብር 22,723,053.64 ከውስጥ ገቢ ብር 24,762,558.02 በድምሩ ብር 48,485,611.66 ከ1996 እስከ 2009 በጀት ዓመት በቅድሚያ ክፍያ የተመዘገበ ሂሳብ /ከ6ወር እስከ 14 ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተከፈለና በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም

ከመደበኛ ሂሳብ

- በ4203 በቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ሂሳብ ብር 1,959,707.15 /ከ2001-2008/ ከ2ዓመት እስከ 9 ዓመት የቆየ መሆኑ፤

ከውስጥ ገቢ ሂሳብ

- በ4203 ግለሰቦች እና ድርጅቶች የተከፈለና ያልተወራረደ ሂሳብ ብር **6,342,450.15 /2008-2009/ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት**

ከመደበኛ ሂሳብ

- በ4210 ሂሳብ መደብ በተቋሙ ሥር ከሚገኙ ዋናውን ግቢ ጨምሮ 2 ኢንስቲትዩት 4 ኮሌጆች 1ሪፈራል ሆስፒታል ብር 3,063,176.46 /ከ2008-2009/ /ከ6ወርእስከ 1ዓመት/

ከውስጥ ገቢሂሳብ

- በ4210 ሂሳብ መደብ 17,740,966.30 2008-2009 ከ6ወር እስከ 1 ዓመት

ከመደበኛ ሂሳብ

- በ4211 ሂሳብ መደብ መደብ-ለግዥ ሠራተኞች የሚሰጥ ቅድመ -ክፍያ ብር 742,624.52

በተቋሙ ሥር ከሚገኙ 2 ኢንስቲትዩት 8 ኮሌጆች 78 ሠራተኞች መካከል 48 ከለቀቁ ሠራተኞች የሚፈለግ የቅድሚያ ክፍያ ብር 399,965.03 ከ1 በሞት ከተለየ ሠራተኛ የተመዘገበ የቅድመ-ክፍያ ሂሳብ ብር 1,317.10 ይገኙበታል፡፡ /ከ1996-2008/ ከ2 ዓመት እስከ 14 ዓመት

ከውስጥ ገቢ ሂሳብ

- በ4211 የሂሳብ መደብ-ለግዥ ሠራተኞች የሚሰጥ ቅድመ -ክፍያ ብር 537,888.57

  /ከ2008-2009/ ከ6ወር እስከ 1ዓመት
- በ4251 የሂሳብ መደብ ለግንባታ በቅድመ-ክፍያ ሂሳብ የተከፈለ ለኢትዮ ቴሌኮም/ETHIO TELECOM/ በተቀጽላ ሌጀር ቁጥር E02 ብር 5,201,563.41 በ2003 በጀት ዓመት/7 ዓመት/

- ለትግራይ ውኃ ሥራ ኢንተርፕራይዝ/TIGRAY WATER ENTERPRISE/ /በተቀጽላ ሌጀር ቁጥር TO4 ብር 8,594,588.40 በጀትዓመት በ2003 /7ዓመት/ ድምር ብር 13,796,151.81

ከውስጥ ገቢ ሂሳብ

- ➢ በ4253 የሂሳብ መደብ ለአቅራቢዎች የሚከፈል ቅድመ-ክፍያ ብር 141,253.00 ከ2008-2009 ከ6ወር እስከ 1ዓመት

ከመደበኛ ሂሳብ

በ4254 የሂሳብ መደብ /OTHER ADVANCE/ REFERAL HOSPITAL/COLLEGE OF HEALTH SCIENCE/ብር 4,161,393.70 በ2009 በጀት ዓመት ከ6 ወር በላይ የቆየ ሂሳብ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ብር 48,485,611.66 /ከ6ወር እስከ 14 ዓመት/ ባለ ጊዜ ውስጥ በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተከፈለና በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

<u>4.1.2. ስጋት</u>

- የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዲፈጠር ሊያደርግና ሂሳቡ ሊሰበሰብ ወደ ማይችልበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡
- በመንግሥት ታምኖባቸው የወጡ ሕጎች ፤ደንቦች ፤የአፈፃፀም መመሪያዎች ተፈፃሚ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

<u>4.1.3.የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የቅድመ ክፍያ ሂሳቦች ገንዘብ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲወራረዱ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ተሰብሳቢ ተብሎ 4203፤ 4210፤ 4111 ብር 10483818.00 የሚታየው የነበረው መሰብሰብ የነበረበት በ2010 በጀት ዓመት የሚሰበሰብ ሲሆን መሰብሰብ የማይቻለውን በማስወሰን መሰብሰብ የሚቻለው ደግሞ በመሰብሰብ እንዲሰረዝ እናደርጋለን፡፡
- በ4251 የሚታይ ተሰብሳቢ ብር 5,201,563.41 የተወራረደ ሲሆን ብር 8594788.40 ደግሞ የክፍያ ሰርተፊኬት ተዘጋጅቶለት በ2010 እንዲወራረድ ይደረጋል፡፡

4.1.5 **<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

ተወራርዷል የተባለው ሂሳብ መወራረዱን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

4.2. የዋስትና ማስያዣ የጊዜ ገደብን በተመለከተ ፡-

4.2.1. ግኝት

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል ሰባት አንቀጽ30 በንዑስ አንቀጽ 1በፊደል (ለ) (ሐ) (መ) የመንግሥት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን እና የመንግሥት መ/ቤቱን ጥቅም መከበራቸውን እና የመንግሥት መ/ቤቱ ግዴታዎችን የተፈፀሙ መሆኑን መረጋገጥ እንደሚገባቸው በተደነገገው መሠረት

- ❖ የተያዙ ዋስትናዎች ፤ዋራንቲዎች ተገቢውን ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፡-
- ❖ በውሉ መሠረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን ፤ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሠረት አገልግሎት መገኘቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

ተቋሙ ለግንባታ ሥራ ለ1 ሥራ ተቋራጭ ፤ ለ1አማካሪ መሐንዲስ ፤ ለ1 ዕቃ አቅራቢ ድርጅት በድምሩ ብር 13,147,342.97 ለተከፈለ ቅድመ-ክፍያ የዋስትና ማስያዣ /ማስከበሪያ/MAY3, 2001 (ሚያዝያ 25,2003 ዓ.ም እስከ NOVEMBER,2012 (ህዳር, 2005ዓ.ም) ገንዘብ ብር 13,235,517.65 የቀረበው የጊዜ ገደቡ ያለፈ መሆኑን እና በውሉ መሠረት አቅራቢዎቹ ላልሰጡት አገልግሎት፤ ላላጠናቀቁት ሥራ በሕግ የተጠየቁበት እና ውሳኔ የተገኘበት ማስረጃ የተቋሙን ጥቅም ከማስከበር አንፃር በውል ተቀባይ ተዋዋይ ወገኖች ላይ የተወሰደ እርምጃ ባለመኖሩ ሂሳቡ ከ5 ዓመት እስከ 9 ዓመት በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዙን በኦዲታችን ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.2.2 ስጋት

በመንግሥት ታምኖባቸው የውጡ ሕጎች፤ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

- ❖ የመንግሥት ሀብትና ንብረት ያለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

4.2.3. የማሻሻያ ሀሳብ

- ❖ በውል የተገቡ ግዴታዎችን ተፈፃሚ ማድረግ ይገባል፡፡
- ❖ የመ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ በሕግ የተቋሙ ጥቅም እንዲከበርለት ማድረግ ይገባል፡፡
- ❖ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊውን ውሳኔ በወቅቱ ማስተላለፍ ይገባል፡፡

4.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተጠቀሱት ድርጅቶች የመንግስት መስሪያ ቤቶች በመሆናቸው ዋስትና ማስያዝ አላስፈለገም፡፡

4.3 መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን የታየ የተሰብሳቢ ሂሳብ

4.3.1.ግኝት

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ሁኔታ ተገኝቷል፡፡

በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል በ4210 ሂሳብ መደብ ተቀጽላ ሌጀር ቁጥር D01 በ2009 በጀት ዓመት በመክፈቻ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲዞር እና በተዘጋ የሂሳብ ሪፖርት በመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የሂሳብ ምዝገባ ላይ ብር 6,937.43 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሂሳብ ሚዛን መታየት የሚገባው በክሬዲት የሂሳብ ሚዛን መታየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4.3.2.ስጋት

የሂሳቡን ትክክለኛ ገጽታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4.3.3.የማሻሻያ ሃሳብ የማሻሻያ

ተገቢው ማስረጃ ተያይዞ በመደበኛው የሂሳብ ሚዛን እንዲታይ ማድረግ ይገባል፡፡አስፈላጊውን ማስተካከያ መሠራት ይኖርበታል፡፡

5.1. የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ሂሳብን በተመለከተ፣

5.1.1.ግኝት

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ከ6 ወር እስከ 13 ዓመት ድረስ ያሉ ተከፋይ ሂሳቦች ከመደበኛ ሂሳብ ብር 17,361,577.02 ከውስጥ ገቢ ብር 265,322.01 በድምሩ ብር 17,626,899.03 በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

ከመደበኛ ሂሳብ

- ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች በ5002 ሂሳብ መደብ ዋናውን ግቢ ጨምሮ በተቋሙ ሥር የሚገኙ ኮሌጆች /ኢንስትዩት/ ሪፈራል ሆስፒታል ብር 4,065,208.11/ ከ2007 እስከ 2009/ ከ1 ዓመት እስከ 3 ዓመት፤

ከመደበኛ ሂሳብ

የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ በ5004 ሂሳብ መደብ

- በBUSINESS &ECONOMICS COLLEGE ብር 10,305.75 በ2006 በጀት ዓመት/4 ዓመት /፤

- በMEKELLE TECHNOLOGY INSTITUTE ብር 12,897.08 በ2006 በጀት ዓመት /4 ዓመት /፤
- በCOLLEGE OF VETENARY MEDICINE ብር 9,294.67 በ2009 በጀት ዓመት/ ከ6 ወር በላይ፤
- በAYDER REFERAL HOSPITALብር9,904.58 በ2009ከ6 ወር በላይ
- በCOLLEGE OF HEALTH SCIENCE.ብር 119,343.48 በ2009 በጀት ዓመት/ ከ6 ወር በላይ በድምር ብር 161,745.56፤

ከውስጥ ገቢ ሂሳብ

- ❖ ዊዝሆልዲንግ ታክስ/ቅድመ-ታክስ /በ5006 ሂሳብ መደብ ብር 5,923,35 /2008-2009/ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት
- ❖ በመንግሥት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች በ5028 ሂሳብ መደብ ብር 148,474.75 /2008-2009/ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት
- ❖ ሌሎች የመያዣ ሂሳቦች /Other Deposits/ በ5054 ሂሳብ መደብ ብር 110,923..91 /ከ2008-2009/ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት
- ❖ በ5061 ሂሳብ መደብ -የኮንትራት መያዣዎች ሂሳብ (ለግንባታ ሥራ) ብር 13,134,623.35 ከሁለት ዓመት እስከ ስምንት ዓመት የቆየ መሆኑ፤

<u>5.1.2 ስጋት</u>

ግዴታ የተገባባቸው ሂሳቦች በወቅቱ ማወራረድ ካልተቻለ ተጨማሪ ወጪን ሊያስከትልና ለቅጣትም ሊዳርግ ይችላል፡፡

<u>5.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግዴታ የተገባበቸው ሂሳቦች ገንዘብ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲወራረዱየእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ❖ በልዩልዩ ተከፋይ የሚታየው ብር 3,038,399.45 ለሚመለከተው የተከፈለ ሲሆን ቀሪው የክፍያ ጥያቄነ ሲቀርብ የሚከፈል ይሆናል፡፡ ካልሆነ ግን ወደ መንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡
- ❖ በ5004 የሚታየው ተከፋይ ክፍያው ተፈፅሟል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

<u>5.2 የተቀጽላ ሌጀር የሌለው ተከፋይ ሂሳብ</u>

<u>5.2.1.ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 143,352.96 የተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ተቀጽላ ሌጀር የሌለው ተከፋይ ሂሳብ

- **በጤና ሳይንስ እና ሕክምና ኮሌጅ**

በ5004 የተጣራ ደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ብር 119,343.48

- **በዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል**

የደመወዝ ተከፋይ በሂሳብ መደብ 5004 ብር 9,904.58

በ5006 ሂሳብ መደብ ብር 14,104.90 በድምር 24,009.48 በ 2009 በጀት ዓመት በተዘጋ የሂሳብ ሪፖርት በመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የሂሳብ ምዝገባ ላይ መታየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5.2.2.ስጋት

ሂሳቡ ለማን ግዴታ እንደተገባ ላይታወቅ ይችላል፡፡

5.2.3. የማሻሻያ ሀሳብ

የተቀጽላ ሌጀር ለተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲኖራቸው በማድረግ ግዴታ የተገባላቸውን ባለመብቶች ተለይተው እንዲታወቁ ማድረግ ይገባል፡፡

5.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለሰራተኞ ደመወዛቸውን ለመክፈል በተላከው ፐሮል መሰረት በተለያዩ የሂሳብ ቁጥር ችግር ምክንያት የተመለሰ መሆኑን ይታወቃል ሆኖምግ ለቀጣይ ከተቀፅላ ለጀር ምዝገባ እንደምንሰራ ለማሳወቅ እንወዳለን በማለት ገልፀዋል፡፡

5.3.1. መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን የታየ ተከፋይ ሂሳብ

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ሁኔታ ተገኝቷል፡፡

ከመደበኛ ሂሳብ

በዓመታዊ የመዝጊያ ሂሳብ ሪፖርት ላይ እንደሚታየው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ በ5059 ሂሳብ መደብ በክሬዲት ሂሳብ ሚዛን መታየት የሚገባው ሂሳብ ብር 310,757.49 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን ላይ መታየቱ:-

ከውስጥ ገቢ ሂሳብ

በዓመታዊ የመዝጊያ ሂሳብ ሪፖርት ላይ እንደሚታየው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ በ5059 ሂሳብ መደብ በክሬዲት ሂሳብ ሚዛን መታየት የሚገባው ሂሳብ ብር

39,050.00 በድምሩ በዓመታዊ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 349,807.49 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን ላይ መታየቱን ማረጋገጥ ተችሏል።

በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ

- በሂሳብ መደብ 5005 ብር 4,461.55፤
- በሂሳብ መደብ 5006 ብር 8,591.45 በድምሩ ብር 13,053.00 በኮሌጁ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በመደበኛ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት መታየት የሚገባው ሂሳብ በዴቢት የሂሳብ ማዛን ላይ መታየቱን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመቐሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

24.በሂሳብ መደብ 5002 ብር 612,891.96፤

በሂሳብ መደብ 5006 ብር 2,485.42 በድምሩ ብር 615,377.38 በኮሌጁ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በመደበኛ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት መታየት የሚገባው ሂሳብ በዴቢት የሂሳብ ማዛን ላይ መታየቱን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5.2.2 ስጋት

የሂሳቡን ትክክለኛ ገጽታ ላያሣይ ይችላል።

5.3.3.የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሠረት ተከፋይ ሂሳቦችን በመደበኛ የሂሳብ ሚዛን/NORMAL BALANCE ማሳየት ይገባል። እንዲሁም ለተፈጠረውም ስህተት ምክንያቱን በዝርዝር በማሣየት የሂሳብ ማስተካያ ሊሰራለት ይገባል።

5.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በ5059 የበጀት ዓመቱ ባልተጠበቀ የሂሳብ መደብ የሚታየው በስህተት ወደ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድጋሚ ገቢ የተደረገ ሲሆን ተመላሽ እንዲደረግልን ጠይቀናል። ምላሽ ስናገኝ ደረሰኝ የምናቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።

6 የበጀት ሂሣብ

6.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

6.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሦስት ተራ ቁጥር 02(1) መሠረት ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር የበጀትመቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም የተዘረጋ የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ሥርዓት አመዘጋገብ ሊኖረውና በዚያው መሰረት ሊቆጣጠር እንደሚገባ፤ እንዲሁም በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ተራ. ቁጥር 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ

መፈፀም እንደማይቻል በሚደነግገው መሰረት ለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ከተፈቀደው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ ለየአርዕስቱ ከተደለደለው ከ10% በላይ ያልተሰራበት ከመደበኛ በጀት ብር 4,315,360.00፤ ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 1,112,779.76 በአጠቃላይ ብር 5,428,139.76 (13%) ያልተሰራበት፤ እንዲሁም ከመደበኛ በጀት ብር 18,710,110.97፤ ከካፒታል በጀት ብር 1,754,338.25፤ ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 8,917,551.35፤ በድምሩ ብር 29,382,000.57 (11%) ከበጀት በላይ ተጠቅሞ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር --- ተመልክቷል

6.1.2 ስጋት

- የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡
- በመንግሥት ታምኖባቸው የወጡ ሕጎች ፤ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

- የኮሌጁን ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡
- ማናቸውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በቂ በጀት መኖሩን የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ካርድ በማቋቋም ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡ የበጀት እጥረት ሲያጋጥመው የበጀት ዝውውር በማድረግ ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ ችግሩን መቅረፍ ይገባዋል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ዩኒቨርሲቲው ካለው የስራ ጫና አንፃር ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሰኔ ወር ተጨማሪ በጀት በመጠየቅ ላጋጠሙን የበጀት ጉድለቶች የበጀት ማስተካከያ ለማድረግ የበጀት ጭማሪ ጥያቄ አቅርበን መልስ ባለማግኘታችንና በየዓመቱ በኦዲት ግኝት ጥያቄ እየቀረበበት የነበረውን የተሰብሳቢ ሂሳብ ጉዳይ እልባት መስጠት ስለነበረብንና ተወራርዶ ወደ ወጪ በመቀየሩ ምክንያት ነው ፡፡ ስለዚህ በየአመቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መቀጠል ተደጋጋሚ ጥያቄ በማስከተሉና ዩኒቨርሲቲው ይህንን ተሰብሳቢ ሂሳብ ለማወራረድ ሰፊ እንቅስቃሴ የተደረገበት መሆኑ ለመግለፅ እንወዳለን፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

8.ንብረት

8.1. 1.1 አላቂና ቋሚ ዕቃዎች፣

በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት በዩኒቨርስቲው ያለ አገልግሎት በተቀመጡ ቋሚ ንብረቶች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰዱን እንዲሁም በንብረት ሂሳብ ላይ አግባብ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ለቋሚ ንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ መደረጉን፤ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በዓይደር ካምፓስ

- ❖ በዕርዳታ የሚገቡ የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ከሚላኩበት ሀገር /የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች/ ንብረቶቹ ከመላካቸው በፊት የዕቃዎቹ ዓይነት፡ ዋጋ፡ ብዛት የማይታወቅ መሆኑ፡- እንዲሁም በዕርዳታ ገቢ የተደረጉት የሕክምና መገልገያዎች ገቢ በተደረጉበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና ወጪ ተደርገው ለአገልግሎት ዝግጁ በሚሆኑበት ንብረት ወጪ ሞዴል ላይ ዋጋቸው የማይገለጽ መሆኑ፡- ለአብነት ያህል የንብረት ገቢ ደረሰኝ /የሞዴል 19/ ቁጥር 17228 ቀን 08/12/08 የንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር 831099(06/10/08) ፣837559(10/10/08)
- ❖ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተካሄደ ቢሆንም የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች በኮምፒተር ምዝገባ ከተከናወነውና በቢን ካርድ ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ወይም ልዩነት መኖሩን በቆጠራ ኮሚቴው ያልተረጋገጠ መሆኑን፡-

ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች

- ❖ በ PHARMACOLOGY LAB.
    - PCR SET ከአራት ዓመት በላይ
    - VACUUM OVEN
    - ROTARY EVAPORATOR
- ❖ STIMULATION LAB.
    - LAPSIM ከ6 ወር በላይ

ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ሁኔታዎች ንብረቶቹ እንደሚገኙ በተደረገው የኦዲት ቅኝትና ዳሳሳ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በቃላሚኖ ካምፓስ

ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች /በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች/

የምግብ ቤትን በተመለከተ

1 ፍሪጅ ከ4ዓመት በላይ

1 ባለስድስት ምድጃ በኤሌክትሪክ የሚሰራ

2 የወጥ መስሪያ

1 የሻይ ማፍያ

2 የትሪ ማጠቢያ ከ3 ዓመት በላይ

በ PARASITOLOGY LAB.

- MICROSCOPES ከ2 ዓመት በላይ
- +4 REFRINRATOR ከ3 ዓመት በላይ
- INCUBATOR ከ2 ዓመት በላይ

በ VET.PATHOLOGY LAB.

- AUTOMATIC TISSUES
- PROCESSOR
- MICROSCOPES.
- CHEMICALS

በብልሽት ምክንያት ሳይጠገኑ እንዲሁም መወገድ የሚገባቸው ኬሚካሎች ሳይወገዱ ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ሁኔታዎች ንብረቶቹ እንደሚገኙ በተደረገው የኦዲት ቅኝትና ዳሳሳ ለመመልከት ተችሏል፡

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

- ❖ በተማሪዎች ምግብ ቤት በብልሽት ምክንያት 1 ጀኔሬተር ከ2 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ❖ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን ከ4 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ❖ ፍሪጅ 2 ትልቅ 2 መካለኛ 1 ትንሽ በድምሩ 5 ከ4 ዓመት በላይ የቆመ መሆኑ፤
- ❖ የሽንኩርት መፍጫ ብዛት 2
- ❖ የእንፋሎት መውጫ ብዛት 1 ከ4 ዓመት በላይ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸውን በተደረገው የኦዲት ቅኝትና ዳሳሳ ለመመልከት ተችሏል፡

  የንብረት ቆጠራን በተመለከተ

- ❖ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም ከመዝገብ ጋር ያለተገናዘበ መሆኑ፡-
- ❖ የመጽሐፍት ቆጠራ በዓመታዊው የኢንስቲትዩቱ የንብረት ቆጠራ ያልተካተተ መሆኑ፡-

የንብረት ክምችትን በተመለከተ

- ለማጽጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች ኦሞ፤ ፊሊት የመሳሰሉት በብዛት ተከማችተው በንብረት መጋዘን መገኘታቸው፤ በኦዲት ቅኝትና ዳሰሳ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ንብረቶች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

8.1.1.2 ስጋት

ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

8.1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ንብረቶቹ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይገባል፡፡

8.1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የሸንኩርት መፍጫ ማሽን እና የመሳሰሉ ማሽነሪዎች መወገድ ሲገባቸው ያልተወገዱ ተከማችተው እንዳሉ በግኝቱ ላይ ተገልፀዋል። ስለዚህ እነኚህ ማሽኖች እና ሌሎች ተመሳሳይ ማሽኖች በትክክል ተከማችተው ይገኛሉ። ሰለዚህ እነኚህ ማሽኖች በዩኒቨርሲቲያችን አቅም መወገድ የማይችሉ መሆናቸውና የማስወገድ ስልጣን የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መሆኑን እየገለፅን በኛ በኩል ማሽን ነክ የሆኑ እቃዎች ማስወገድ የማንችል መሆናችንን ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በህዳር 8/2010 ዓ/ም የተፃፈልን ደብዳቤ እና ዩኒቨርሲቲያችንም በቅርቡ እንዲያስወግድልን ወይም መፍትሄ እንዲሰጠን በሚል የፃፍነው ደብዳቤ ለማሳያነት ያክል በኮፒ አያይዘን አቅርበናል በመሆኑም በዚህ ሁኔታ የማስወገድ ስልጣን የሌለን መሆና ንብረቶቹ ተከማችተው እንዲቆዩ ተብሎ በተሰጠን ሰርኩላር ደብዳቤ መሰረት አዘጋጅተን ያስቀመጥን መሆናችን በመገንዘብ ግኝቱ እንዲሰረዝልን እንጠይቃለን ።
- PCR SET ፣ ማይክሮባይሎጂ ላብራቶሪ የሚገኝ ሲሆን በየወቅቱ ለተማሪዎች ስልጠና አገልግሎት የሚሰጥበት ማሽን መሆኑ
- VACUUM OVEN ፣ በፋርማኮግኖኪ እና ፋርማሴውቲካል አናሊስስ ላብራቶሪ የሚገኝ እቃ ሲሆን እቃው ምንም ዓይነት ችግር የሌለበት መሆኑንና በባለሙ.ያ ታይቶ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡
- ROTARY EVAPORATOR ፣ በፋርማኮግኖኪ እና ፋርማሴውቲካል አናሊስ ላብራቶሪ የሚገኝ ሲሆን በወቅቱ ጊዚያዊ ብልሽት አጋጥሞት የነበረ ሲሆን የተበላሸው እቃ በግዢ ሂደት ላይ መሆኑና በላብራቶሪው ካሉት እቃዎች ውስጥ ብዙ አገልግሎት የሚሰጥ መሳሪያ መሆኑን
- LAP SIM (STIMULATION LAB)፣ የተባለ እቃ በፋርማኮሎጂ ላብራቶሪ የሚገኝ አዲስና በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤

- በብልሽት ምክንያት ያለ አገልግሎት የተቀመጠ ጀነሬተር በተመለከተ፡-በግኝቱ ላይ የተገለፀው ጀነሬተሩ ተበላሽቶ ከሁለት ዓመት በላይ የቆመ እንደሆነ ይገልፃል ።ነገር ግን ጀነሬተሩ እስከ ሚያዝያ ወር 2009 ዓ/ም እየሰራ የነበረ መሆኑን እና ከግንቦት 14/2010 ዓ/ም ጀምሮ ግን በአገልግሎት ብዛት ምክንያት ተበላሽቶ የቆመ መሆኑን ለዚህም ጥገና እንዲደረግለት የተጠየቀ መሆኑን እና የብልሽቱ ዓይነትም በባለሙያ ፍተሻ እንዲደረግበት በማድረግ ለጀነሬተሩ የሚያስፈልጉ የመለዋወጫ እቃዎች ግዥ እንዲፈፀምለት የተጠየቀ መሆኑን። በዚህ መሰረትም ለጀነሬተሩ የሚያሰፈልገው መለዋወጫ እቃ እንዲገዛ በግልፅ ጨረታ በማዉጣት አሸናፊ ድርጅትም በመለየት ውል የታሰረ መሆኑን እና ንብረቱ በመግባት ላይ ያለ መሆኑን እያሳወቅን ልክ ንብረቱ እንደገባ በማስገጠም ጀነሬተሩ መልሶ ጥቅም ላይ የምናዉለው መሆናችንን እየገለፅን ለጀነሬተሩ የሚያስፈልጉ የተጠየቀው የመለዋወጫ እቃዎች የግዥ ጥያቄ እና አሸናፊው ደርጅት ዉል ያሰረበት ዉል ለማሳያነት ያክል አያይዘን ስንልክ ጀነሬተሩ ግን ለሁለት ዓመት ሳይሆን ተበላሽቶ የቆመው ለ7 ወር ብቻ መሆኑን እየገለፅን አሁን ግን እቃዎቹ በግዚያዊነት ገቢ የተደረጉ ሲሆን ጥራቱ በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጎ የጀነሬተሩ ጥገና በማድረግ ስራ የሚጀምር መሆኑ እናሳውቃለን።
- ፍሪጆች በተመለከተ ፡-ፍሪጆች በተለያዩ ምክንያቶች ተበላሽተው የቆሙ ሲሆኑ አሁን ግን የብልሽታቸው ምክንያት በማጥናት ተጠግነው ዳግም ስራ ላይ እንዲዉሉ ለማድረግ ጥረት እያደረግን ሲሆን መወገድ የሚገባቸው የማስወገድ ስራ የምንሰራበት መሆናችን ።
- መኖርያ የሆኑና መኖርያ ያልሆኑ የዩኒቨርሲቲው ህንፃዎች በተመለከተ፡-መኖርያ የሆኑና መኖርያ ያልሆኑ ህንፃዎች እንደቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ ያልተመዘገበ መሆኑን ለሚለው ትክክል እሰከ አሁን ድረስ በቋሚ መዝገብ ያልተመዘገበ መሆኑንና አሁን ግን ኮሚቴ በማቋቋም ለመመዝገብ በዝግጅት ላይ ያለን መሆናችንን እየገለፅን የተቋቋመው የህንፃ ቆጠራ ኮሚቴ ለማሳያነት ያክል ደብዳቤው አያይዘን አቅርበናል ።
- በኢትዮጵያ ኢንስቲቱት ቴክኖሎጂ ፣በተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ፣ በቢዝነስ ኮሌጅ በዎርክሾፖችና በተማሪዎች ምግብ ቤት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መወገድ ያለባቸው ማሽኖች ስለመኖራቸው በተመለከተ ከላይ እንደገለፅነው ማሽን ነክ የሆነ ንብረቶች በዩኒቨርሲቲያችን መወገድ አንደሌለበት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ራሱ እንደሚያሰወግዳቸው የሚታወቅ ሲሆን ለማሳያ ህዳር 8/2010 የፃፉልን ደብዳቤ ማሽን ነክ የሆኑ ንብረቶች በኛ በኩል መወገድ እንደሌለባቸው ነገር ግን ዝርዝራቸው እንድንልክላቸው በጠየቁን መሰረት የላክንላቸው ሲሆን ለማሳያነት ያክል አያይዘን አቅርበናል። (አባሪ ቁጥር09 የሚወገዱ ንብረቶች በተመለከተ ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ የተላከ ደብዳቤ እና ሌሎች የንብረት ግኝት የሚመለከት የቀረቡ ማስረጃዎች አሉን የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

የተሽከርካሪ አያያዝን በተመለከተ

7.2.1.ግኝት.

የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪዎች በፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ❖ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ልኬታቸው /ጌጅ/የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ብዛት 36 /ሠላሳ ስድስት/የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ /የሌላቸው ብዛት 44 /አርባ አራት/
- ❖ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪ ኮድ ያልሆኑና የተቋሙ ንብረት ስለመሆናቸው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ብዛት 15 /አስራ አምስት/
- ❖ የሠሌዳ ቁጥር እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ብዛት 2/ሁለት/ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ዝርዝሩ ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 22 ተመልክቷል፡፡

7.2.2 .ስጋት

- የመንግሥት ሀብትና ንብረት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- የባለቤትነትን መብትና ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

7.2.3 .የማሻሻያ ሀሳብ

የተሽከርካሪዎቹን ጌጅ /ልኬት/ ጥገና እና የልኬት መሣሪያውን እንዲገጠም በማድረግ የነዳጅ አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግ ይገባል፡፡

7.3. 4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ➢ የሠሌዳ ቁጥር እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው የተባለው ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ተፅፏል፡፡ አባሪ ተያይዟል 10
- ➢ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ልኬታቸው /ጌጅ/የማይሰራ ተሽከርካሪዎች የሚለው እስከ አሁን ድረስ 16 ተሰርቶላቸዋል፡፡ አባሪ ተያይዟል 11
- ➢ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪ ኮድ ያልሆኑና የተቋሙ ንብረት ስለመሆናቸው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ለሚመለከተው አካል ጥያቄ አቅርበናል፡፡

8.ልዩ ልዩ

8.1. የፍትሐ-ብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ

8.1.1.ግኝት

ለተቋሙ የህግ አገልግሎት በተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለማስመለስ በስራ ክፍሉ ተገቢው ክትትል እየተደረገ መሆኑንና ጉዳዮቹም የሚገኙበትን ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ለህግ ክፍል ተመርተው ክስ ያልተመሰረተባቸው ጉዳዮች

በዋናው ግቢ

ለተቋሙ የህግ አገልግሎት በተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለማስመለስ በስራ ክፍሉ ተገቢውን ክትትል እየተደረገ መሆኑንና ጉዳዮቹም የሚገኙበትን ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ ወደ ተለያዩ ተቋማት ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሰረት ባለመፈፀማቸው (1) ለአንድ መምህር የሚፈለግበትን የዕዳው መጠን ገና ያልታወቀ ፤32 መምህራን ደግሞ ብር 3,490,312.00 ጉዳዩ ለህግ አገልግሎት የተመሩ ቢሆንም ክስ ሳይመሰረትባቸው ያለምንም እርምጃ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ **ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 23 ተመልክቷል፡፡**

8.1.2. **ስጋት፣**

- በባለዕዳዎች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ የመንግሥት ገንዘብና ንብረት ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲውል ዕድል የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር ገንዘቡ እና ንብረቱ ወደ ማይሰበሰብበት ደረጃ ሊያደርስና ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዲከሰት መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡
- የተቋሙን ጥቅምም ሊያሳጣ ይችላል ፡፡

8.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ተቋሙ በወቅቱ ክስ ያልተመሰረተባቸው ባለጉዳዩች ላይ ጥቅም ከማስከበር አንጻር ህጋዊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በዩኒቨርሲቲው የተወሰኑት በውሳኔው መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የሚመለከተው የስራ ክፍል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8.4.1 **በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ እርምጃ አለመወሰዱን በተመለከተ**

- ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢዎች በውላቸው መሠረት ሳያስረክቡ ላዘገዩበት አቅራቢዎች ገቢ መሆን የነበረበት ብር 793,337.87 የጉዳት ካሳ ለመንግሥት ገቢ አለመደረጉ
- ብር 80,624.00 ገንዘብ መከፈሉን የሚያረጋግጥ የሽያጭ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (credit sales invoice) ብቻ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ማስረጃ ስለቀረበ የተቀነሰ አ<ን>ጋዝ/የተስተካከለ አ<ን>ጋዝ/ቁጥር
- ብር 324,490.70 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብት ሂሳቡ ተወራርድ የተገኘ መሆኑ፡-

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የብር 68000.00 ደረሰኝ ተያይዟል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የቀረበው ማስረጃ ብር-47,000.00 ብቻ መሆኑን እናረጋግጣለን!

- ❖ አላአግባብ የ2006 እና የ2007 ዓ.ም የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ብር 29,564.40 የተሰጠ መሆኑ
- ❖ <u>በመቀሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት</u> ለውሎ አበል እና ለሌሎች ጉዳዮች ማስፈጸሚያ በሚል ገንዘብ ብር 2,521.10 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፡-
- ❖ ቅድመ ገቢ ግብርና ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 34,807.35 ሳይቀነስ ክፍያ መፈፀሙ
- ❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 446122 የመድሃኒት ግዥ ክፍያ ሲፈጸም የብር 243,890.00 መድሃኒቶች የግዥው ዘዴ የተከናወነበትና ውል የተፈጸመበት ማስረጃ ሳይቀርብ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ቁጥሮች 18043 እና 16523 mannitol salt agar 50gm, Metris 100ml እና ECG paper for schiler (AT-102) ገቢ ተደርገው ክፍያ ተፈጽሞባቸው መገኘቱ፡-

- ❖ ተቋሙ የአሳተመው አጀንዳ ጥራቱን ያልጠበቀ መሆኑን የተገለፀ ቢሆንም አጀንዳው በሙሉ ገቢ ተደርጎ ለአገልግሎት እንዲሰራጭ በተወሰነው መሠረት በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 285692 ብር 1,071,984.00 ክፍያ ተፈጽሞበት መገኘቱ
- ❖ ተቋሙ ከትግራይ ክልል ጤና ቢሮ ባደረጉት ስምምነት መሰረት ፕሮግራሙን ላስተባበሩ ለተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊዎችና የአስተዳደር ክፍል ሰራተኞች ተጨማሪ የስራ ጫና /Overload/ በሚል ብር 999,756.00 ከዩኒቨርሲቲው ቦርድ ፈቃድና ዕዉቅና ውጪ የተከፈለ መሆኑን

በ2007 በጀት አመት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች

- ❖ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር ለደመወዝ ሂሳብ ኦዲት በተወሰደ ናሙና መሠረት፣በ2007 በጀት አመት በዋናው ግቢ ለውጭ ሀገር መምህራን ከተከፈለው ደመወዝ ብር 1,647,835.55 ላይ ብር 552,229.94 የሥራ ግብር ተቀናሽ መደረግ ሲገባው ተቀናሽ ያልተደረገበት መሆኑ፣
- ❖ በዋናው ግቢ በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት ሂሳቦች መካከል ለ1 የውጪ ሀገር መምህር የታህሳስ/2007፣ የሚያዝያ/2007፣ የግንቦት/2007 እና የሰኔ/2007 ደመወዝና የቤት አበል በትምህርት ዝግጅታቸውና ማዕረጋቸው መሠረት ብር 311,906.73 (15,100 ዶላር) መከፈል ሲገባ ብር 398,662.25 (19,300 ዶላር) በመከፈሉ በብልጫ ብር 86,755.52 (4,200 ዶላር)የተከፈለ መሆኑ፣

- ❖ በትርፍ ሰአት ላስተማሩ መምህራን የተከፈላቸው ሂሳብ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ጠ.ሚ ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት መሆኑ ሲጣራ፡-በድምሩ ብር 610,372.00 ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣

- ❖ ሚያዝያ 20/1990 በቁጥር 80-አጠ52/01/09 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተላለፈው መመሪያ መሠረት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ለትምህርት ወይም ሥልጠና ተልከው ትምህርታቸውን ስለሚከታተሉ ሠራተኞች የቤት አበል ጉዳይ ሳይጠቀስና ስለ ደመወዝ አከፋፈል ብቻ ተጠቅሶ እያለ **በተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ**በውጪ ሀገር በትምህርት ላይ ላሉ 15 መምህራን ለእያንዳንዳቸው በወር ከብር 800.00 እስከ ብር 1,000.00፣ በድምሩ ብር 26,800.00 በመመሪያ ያልተደገፈ የቤት አበል የተከፈላቸው መሆኑ፣
    - ❖ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 38,739.00 የውሎ አበል ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
    - ❖ የተማሪዎች ህብረት እስከ መጋቢት/2007 ከተለያዩ የውስጥ ገቢዎች ሰብስቦ ሲጠቀምበት የነበረ ሲሆን ከመጋቢት/2007 በፊት በህብረቱ የተሰበሰበው የገቢ መጠን ኦዲት ሳይደረግና ከወጪ ቀሪው ሳይታወቅ በባንክ እና በእጅ የነበረ በድምሩ ብር **529,361.20** ወደ ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ መደረጉ፣
- ❖ ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ግንባታዎች ከኮንትራክተሮች ጋር በገባው ውል መሠረት ግንባታዎቹ ሳይጠናቀቁ ለዘገዩበት ዩኒቨርሲቲው ለደረሰበት ጉዳት /liquidation damage/ ከ5 ኮንትራክተሮች ማግኘት የሚገባው እስከ ዋናው ውል 10% ድረስ በየቀኑ የውሎቹ 1/1000ኛ (0.001) ተሰልቶ የ4 ግንባታ ፕሮጀክቶች ከዉሉ ጠቅላላ ዋጋ ብር 78,289,582.20 ላይ ብር 7,828,958.22 የጉዳት ካሳ ለመንግሥት ገቢ በዩኒቨርሲቲው የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ ድረስ የተሟላ እርምጃ አለመወሰዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.4.2 ስጋት፣

ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ተቋሙ በኦዲት ሪፖርት ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች አብዛኞቹ ተግባራዊ አለማድረጉ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋትና መጉደል መንገድ የሚከፍት አሠራር ሲሆን፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

8.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የአሠራር ግድፈቶቹ ለገንዘብና ንብረት መጥፋትና መጉደል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አሠራሮች በመሆናቸው በጉዳዮቹ ላይ ተቋሙ እርምጃ እንዲወስድ በድጋሚ እሳስባለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!